# የአንድነት ዘመን እና ምልክቱ

ደህና አመሻቹ። ዛሬ ማታ እዚህ መገኘት፡ እና እዚህ ስፍራ መቆም መታደል ነው።

2 ዛሬ፡ ጠዋት፡ ስመጣ በመንገድ ላይ... ጌታን ስጠባበቅ፡ ጸሎት ላይ ነበርኩ። መንገድ ላይ ሳለሁም፡ የጥቁሩ ወንድማችን፡ወንድም ስሚዝ፡ የሬድዮ አገልግሎት—ከፍቼ (ዛሬ ጠዋት አዳምጣችሁታል? ያዳመጠ ሰው አለ?) ከ፡ ከኦሃዮ ይመስለኛል። እየሰበከ ነው ብሎ ብለውኝ፡ እንደው፡ “መክፈት አለብህ፡” ብሎኝ ነበር።

3 እንደው አጋጣሚ ሆኖ፡ ዛሬ ጠዋት ከፈትኩ። ኃጢአት በዓለም እንዴት እንደበዛ አስረግጦ ሲናገር ነበር፡ ከዚያም እሱን... አለፍ ብየ ቀጠልኩና፡ ሌላ ጣብያ ከፍቼ፡ እንደገናም ሌላኛውን ሰማሁ። እዚህ ስደርስ፡ ተዘጋጅቼ ነበር፡ ጠዋት እዚህ ስገባ፡ ቤተ ክርስቲያን ለመድረስ ካላረፈድኩ እስኪ አስታውሱት። ስለዚህ፡ ዛሬ ማታ እዚህ መገኘት፡ እና በጌታ አገልግሎት መሆን በእውነት መታደል ነው።

4 በቀደም ለት ስለ ወንድም ነቪል፡ እና ስለ መልዕክቱ ስናወራ፡ ያቺን ምስኪን ሴት፡ ተለይታን የሄደች እህታችንን በተመለከተ ስንነጋገር። እህት ዊቨር፡ ማን እንደሆነች፡ ሁላችንም እናውቃታለን። እና ዛሬ ስለተጠመቀው ሰውየ፡ እያሰብኩ ሳለሁ፡ ገንዳው ውስጥ እሷን... ያጠምቅኳት እኔ ነኝና... በዊልቸር ነበር ያመጧት። በካንሰር ምክንያት፡ በሞት አፋፍ ድርሳ ነበር፡ በህይወት ለመኖር ያቺ ምሽት ቀርታት ነበር፡ ዶክተሮቹ ተስፋ ቆርጠውባታል፡ በነጋታው ልትሞት ነበር። ወደ ቤቷ ሄጄ ስለ መለኮታዊ ፈውስ ልነግራት ሞከርኩና፡ ደጋግማ እንዲህ ትናገር ነበር፦ “አንተ ወደ ቤቴ ጣራ ስር እንድትገባ የሚገባኝ ሰው አይደለሁም።” “እኔ’ኮ—አገልጋይ ከጣርያዬ በታች እንዲገባ የሚገባኝ ሰው አይደለሁም፡” ትላለች። “እኔ’ኮ ኃጢአተኛ ነኝ፡” ትል ነበረች። ግን ደግሞ እንዲህ አለችኝ፦ “ጌታየ፡ እኔ በዚህ አይነት ሁኔታ መሞት አልፈልግም።” ወደሷ የወሰደችኝ፡ እዚያ ያለችው፡ ግሬስ ዊበር ናት። ከአገልግሎት ብዛት፡ እጅግ ደክሞኝ ነበር የመጣሁት፡ ቃል እያነበብኩላት፡ በጸለይኩላት ጊዜ ግን፡ ዳነች። ወድያው፡ እራሷን ቀና ማድረግ ባትችልም፡ የሁላችንም እጅ መጨበጥ ግን ፈለገች። እንደው... የሆነ ነገር ሆኖላታል።

5 እጅ እየተጨባበጡ ሳሉ ራዕይ አየሁ፡ ወደ ደሮዎች ስፈር ሄዳ፡ ስትመለስ አየኋት። “በጣም ጥሩ፡ አሁን መልካም ይሆናል”፡ አልኳቸው፡ የዛሬ አስራ ስምንት ዓመት ነው። እና ይሄን ሁሉ ዓመታት፡ ካንሰሩን አሸንፋ ቆይታለች። ከሞተችም... መቼም በካንሰር አልሞተችም፣ የገደላት የልብ ድካም ነው። ኦክስጅን ገጥመውባት ነበር፡ የሞተችው በልብ ድካም ነው።

6 በስተመጨረሻም ሰዎች ሁሉ፡ **ዘን ጂሰስ ኬም፡** ዘምረው እየወጡ ሳሉ፡ ይሄን እያሰብኩ ነበር። የሆነውም ይሄው ነው፡ መጣና አስራ ስምንት አመታት ሙሉ ጠበቃት። “እንዴት ይደንቃል፡” አልኩኝ። ሲቲቱ እያሸነፈች እንደሆነ

ሳታውቅ አልቀረችም። ከዚያ በኋላም፡ እንደገናም፡ ሊኖርባት ይችል ይሆናል። **ዘን ጂሰስ ኬም** የሚል አዝማች በዚያ መዘመሩ ግን፡ እንዴት ይደንቅ ነበር።

7 ጉባኤ ከመጀመሬ፡ እንደው—ይመስለኛል፡ ትንሽ ቀደም ብሎ ስለነበረ። በጣም ተረበሽኩ። ዛሬ ጠዋት፡ ጥሩ አልነበርኩምና፡ ጸሎት—ለማድረግ ሄድኩኝ። እና—ወደቤት፡ ተመለስኩኝና። ልጆች ትምህርት ቤት መግባት ስላለባቸው፡ እኔም... ቤተሰቤን ሁሉ፡ ወደ አሪዞና ልኬያቸዋለሁ። እንደው እኔም—ትንሽ አረፍ ብየ፡ እዚህ ካሉ ወንድሞች ጋር እና ከነ ወንድም ዉድስ ጋር አደን ለመሄድ ተመለስኩ፡ በሚቀጥለው ሳምንት፡ አደን እንወጣለን። ወደ ኬንታኪ እንሄዳለን። እና እኔም... ሰደርሰ... እንዳጋጣሚ ወይዘሮ/ ዊቨር በሞተችበት—ቀን ደረስኩ፡ እና እዚህ ተገኝቼ ወንድም ኔቪልን በዚያ የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ መርዳት መቻሌ ትክክል ነው።

8 በተጨማሪም... ቅሬታ ስለሚያቀርቡ ሰዎች—ታውቃላችሁ፡ ብዙም ማለት አልፈለግኩም። ምክንያቱ፡ እጅግ አስከፊ ከሚባሉት ነገሮች አንዱ—በተደጋጋሚ ቅሬታን የሚያቀርብ ሴት ወይም ወንድ ማየት ነው። ሁሌም "ጌታ፡ ከዚህ ይሰውረኝ፡" እላለሁ። እያችሁ፡ እናንተም ታውቃላችሁ፡ እንዲህ ያለ ነገር፡ ዘወትር እምነትን ያዳክማል። እናንተ—እናንተ... እናንተም—እናንተም... ይገባኛል እንደው እርጅና ሲመጣ፡ እያንዳንዳችን፡ አንድ ነገር እንዲከሰት እና የሆነ ነገር እንዲፈጠር እናደርጋለን። ዕድሜ እየገፋችሁ ስትሄዱ፡ እነዚህ ጥቃቅን ነገሮች እየተከማቹ እንደሚቀጥሉ አውቃለሁ፡ አይቀሬ ናቸው። እጅግ አስከፊ የሚባለው ነገር ግን፡ ሰይጣን የአንድ ሰው ህይወት ላይ እክሊል ሲጭን ነው፡ እያችሁ፡ አጉረምራሚ ሽማግሌ እና አሮጉት መሆን። የዚያን ያህል እንደማልደርሰ—ተሰፋ አድርጋለሁ። ሸክሜን ለመሸከም፡ ወደዚያ ደረጃ መድረስ፡ የሚችል ሰው—እንድሆን ተሰፋ አደርጋለሁ... የእኔ ህይወት የጌታ የክብር አክሊል እንዲጫንበት እመኛለሁ፡ ትዕግስቱ፣ መልካምነት፣ ሰላም፣ ትህትና፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እሻለሁ።

9 እንደው እኔም... ህይወቴ ሁሉ እጅግ የሚጎዳኝ ነገር ቢኖር፡ ቁጡ መሆኔ ነው። በጣም ስዝል፡ ያኔ እደክማለሁ። እንደምታውቁት... ማንም አያስብልህም፡ ዝም—ብለህ ነህ እንጂ... አንተም ብትሆን፡ አሉብህ፡ ይላችኋል። ታውቃላችሁ፡ አንዳንዴ ኦቨርዶዝ ይሆንብኛል፡ እጅግ ወደ ከፋ ደረጃ ይደርስብኛል፡ መቋቋም አልችልም... ይሄን የሚያመጣው፡ የጫና ብዛት ነው። ብዙ ጊዜ በተለይ ደግሞ፡ ከነዚህ ተደራራቢ ራዕዮች ጋር፡ እያችሁ፡ በጣም ይከብደኛል። አንድን ሰው አየውና፡ "ራዕይ ነው። አይ፡ አይደለም፡ አይደለም፡ ራዕይ አይደለም። አዎን! ራዕይ አይደለም? " ብየ እሰባለሁ፡ እያችሁ? በተጨማሪም ይህ ነገር የሚያስከፍላችሁ ዋጋ አታስተውሉትም። ከዚያ በኋላ—በቃ ከዚያ በኋላ—ግራ ትጋባላችሁ። ከዚያ በኋላ በጣም ታስባላችሁ፡- "በቃ፡ አነተ'ኮ... " ከዚያ በኋላ ራሳችሁን በመጣል እንዲህ ትላላችሁ፡- "እሺ፡ አሁንስ፡ ምን—እስኪ ምን ሰራሁ? እንደው፡ እኔ—ሐምሳ ዓመት ሞላኝ ለጌታም ምንም አልሰራሁም፡ እያረጀሁ—ነው። ታድያ ምንስ... ? ኡህ፡ ማይ።" ከዚያ በኋላ... ምን ብለን ነበር የምንጠራው "ብሉስ" ይይዝሃል። በእኔ ዕድሜ ያላችሁ ወንድሞች ምን ይሉት እንደነበረ "ብሉስ ተይዟል" ይባላል ታስታውሳላችሁ። ፖፕ ይሄን ሲናገር ምን ማለቱ ነው ብየ እገረም ነበር፡ ምን ማለቱ እንደሆነ በርግጥ አሁን ገባኝ። ከዚያ በኋላ፡ ዝም ብላችሁ ሌላ ለመሆን ትጥራላችሁ፡ አንዳች እውነት'ኮ

የለውም፡ ያው እናንተ ናችሁ፡ ደግሞ ታውቁታላችሁ። አያችሁ፡ ታውቁታላችሁ፡ እናንተ ራሳችሁ የምታደርጉት ነው።

10 ስለዚ እስኪ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ዝም ልበልና፡ በቅርብ ጊዜ ለሚመጣው—ነገር ልዘጋጅ ለማለት ሞከርኩኝ። ከዚያም በኋላ... አንድ ጉባኤ፡ ካምፔይን ለማዘጋጀት... በቀጥታ፡ ወደ ኒውዮርክ እመራለሁ። ቀጥሎ ወደ ሽርቪፖርት፡ ከዚያ በኋላ ወደ ፊኒክስ መመለስ። ከዚያ በኋላ ወደ ምዕራብ መምጣት... ወደ ደቡባዊ የዩናይትድ ስቴትስ ድንበር። እና አሁን ምናልባት ከዓመቱ መጀመርያ በኋላ ወድያው ለመጀመር፡ ድንበር ተሻግረን ለመሄድ ቅንጅት በማድረግ ላይ ናቸው፡ ምናልባት መጋቢት፡ ሚያዝያ፡ አካባቢ ላይ፡ ከስቶክሆልም ወይም ኦስሎ ጀምረን፡ ከቻልን ከሚቀጥለው ጉዟችን፡ ዓለምን ሁሉ ለማዳረስ ነው።

11 ስለዚህ አሁን ትንሽ ለማረፍ ያክል፡ ወደ ራሴ ለመመለስ እና እራሴን ለማደስ፡ ወደ ቤት መጥቻለሁ። እና ጌታ ቢፈቅድ፡ ቀጣይ እሁድ፡ ከኬንታኪ እመለሳለሁ። ወንድም—ነቪለን ካላስቸገርኩት፡ ጌታንም ካስደሰተው እና መልካም የሚሆን ከሆነ፡ እንግዲህ፡ ጌታ—ቢፈቅድ፡ በሚቀጥለው እሁድ ለማገልገል እሞክራለሁ። ወንድም ነቪል ፍቃደኛ እንደሆነ ሁሉ፡ እሱም ከፈቀደልኝ፡ እዚህ—እገኛለሁ። አዎን፡ ወዳጄ፡ እሱ ልክ እንደ... እንደ ወንድም ነቪል ፍቃደኛ ከሆነ፡። እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ። አያችሁ፡ አሁን በቅርቡ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ረዘም ላለ ጊዜ ከእናንተ እንደምርቅ አውቃለሁ።

12 እና... በልቤ ውስጥ ያሉት፡ ጥቂት መልዕክቶች፡ እንደው—ለእናንተ—ላካፍል ተሰምቶኛል፡ አያችሁ፡ በዚያ ዙርያ ህብረት እናደርጋለን። ባለፉት ጥቂት ቀናት፡ ጥቂቶቹን፡ ማለት አምስት ወይም ስድስት ያህሉ ተቀብያለሁ። ለሁለት ቀን፡ ሽኮኮን ለማደን፡ ወጥቼ ነበር። ወደ ጫካዎቹ ሄጄ፡ እርሳስ እና ወረቀትም ይዤ ነበር። አያችሁ? ልክ የቀኑ ጸሀይ ጠንከር በሚልበት ጊዜ፡ ከአንድ ዛፍ በታች አረፍ እላለሁ። እንቅልፍ ካልወሰደኝ፡ መጸለይ እጀምራለሁ፡ ከዚያ በኋላ፡ ጌታ አንዳች ነገር ይሰጠኛል፡ ከተሰጠኝ ነገርም ጥቂት ማስታወሻ እይዛለሁ፡ አያችሁ። ምንን ማለት እንደፈለግኩ አውቃችኋል፡ ወደ ራሳችሁ ስትመለሱ፡ ከዚያ በኋላ... መጥቼ፡ መላ ይዘቱን በወረቀት ታብሌት ላይ አስፍረዋለሁ። ስለዚህ ጥሪ ሲኖረኝ፡ እሄድና ታብሌቴን ገልጬ እፈትሻለሁ ከዚያ በኋላ በምን እንደምጀምር ፍንጭ አያለሁ፡ አያችሁ። አሁን የሆነው ነገርም ይሄው ነው።

13 ስለዚህ አሁን፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ አንድ ነገር... እናገራለሁ፡ ረዘም ያሉትን... አያችሁ፡ ብዙ ሰዓታትን የሚፈጁ፡ ረጃጅም መልዕክቶችን፡ አሳጥራቸዋለሁ። ትናንት ማታ በቺካጎ፡ ምናልባት የሰላሳ ደቂቃ ትሆናለች፡ ጌታ አጠር አድርጌ እንዳቀርብ ረድቶኛል። እና አንድ ሰው ወደ'ኔ መጥቶ፡ እንዲህ አለኝ፦ "በውስጥህ ይኖራል ብየ አላሰብኩም ነበር፡ ግን አደረግከው!" ስለዚህ ከሁለት ተኩል፡ ወይም ሶስት ሰዓታት መካከል፡ ሠላሳ ደቂቃ ማውጣት፡ ማለት። ስለዚህ ምናልባት ዛሬ ማታም ፈጠን ልበልና፡ እናንተን እለማዘግየት፡ ልለማመድ።

14 ጌታ ይባርካችሁ። የትም ብሄድ፡ እንደዚህች ቤተክርስትያን ዓይነት ስፍራ ከየትም አላገኝም። ልክ እንደ ቤት፡ መልካም ቤት ናት። ከዊሸር ቤተሰብ ጋርም ሀዘን ላይ ነኝ። ከሞተው ጥቁሩ ውድ ወንድማችን ጋርም እንዲሁ፡ ከመሞቱ

በፊት አብሬው ጸልያለሁ፡ ደስ የሚል ባህርይ አለው። አሁን ሁሉንም ጨርሷል፡ ከጌታ ጋር ወደ ቤቱ ሄዷል። እኛ ሁላችንም መሄዳችን አይቀርም፡ እናውቀዋለን። ጌታ ነፍሳቸውን ያሳርፍልን፡ እኛም’ኮ... አንድ ቀን ወደዛኛው ምድር እንድንሻገር ተሰፋ እናደርጋለን፡ ህመም፡ ሀዘን፡ ወይም ሞት ወደ ሌለባት ምድር። እስከዚያ ድረስ ግን፡ ለወንጌል የቻልነውን ያህል እናድርግ።

15 ስለ ውጥረት ስንናገር፡ በዚህ ጉዳይ ዛሬ ጠዋት እየጸለይኩበት ነበርኩ። ውጥረት ባይኖርባችሁ ምን ታደርጉ ነበር? አስቡት። ውጥረት የኑሮ አንድ አካል ነው። ይሄን ሳስብ እጅግ ያበረታኛል። ውጥረት ባይኖርባችሁ፡ እንደተጣለች አሻንጉሊት፡ ስሜት አይኖራችሁም ነበር። የምትሰሩት አንዳች ድርጊት አይኖራችሁም ነበር። እንደ ባል እና ሚስት፡ ምናልባት እሷ አንዳች ነገር ማድረግ ብትፈልግ፡ (በተለይ ደግሞ ክርስትያኖች) አብረው ለመስራት ይሞክራሉ፡ ሌላኛው የሚፈልገው ደግሞ... እና ለዚህ ጉዳይ ወደ አንድ ሰትመጡ... የሰራችውን ነገር ታያላችሁ፡ እሷም ታያለች... እያችሁ፡ ውጥረቱ አንድ እንድትሆኑ ያደርጋችኋል። “እሺ፡” አንድ ሰው ሊነግርህ ይችላል፡ እንዲህ ይልሃል፦ “አንተ በመልካም ሳትሆን ሰትቀር ሚስት የምታልፍበትን ውጥረት አሰበው፡” ወይም “አንቺ መልካም ሳትሆኚ ባል በምን ውጥረት እንደሚያልፍ። ከዚያ በኋላ ሁሉንም በይቅርታ ሲታለፍ፡ ሰለሱ የሚሰማሽን ስሜት አሰቢው። አቤት፡ እንደው በቃ... ” እያችሁ፡ ውጥረት ሊኖራችሁ ያሰፈልጋል። ይሄው ነው።

16 እንዲሁም፡ ስለ ስሜት አሰቡት፡ ምንም አይነት ስሜት ባይኖራችሁ፡ ምንም የስቃይ ሰሜት ባይኖራችሁስ? ሰቃይ ብሎ ነገር ባይኖርስ? ምንም አይነት የሀዘኔታ ሰሜት አይኖራችሁም ነበር። እያችሁ? ሀዘኔታ ባይኖራችሁ ኖሮ፡ አንዱ የስሜት ህዋሳችሁ አይኖርም ነበር። እያችሁ? ሰለዚህ፡ እያችሁ፡ ነገር ሁሉ ትክክል ነው። ሰለዚህ፡ “ጌታ ሆይ፡ ይህን መመከት የሚያሰችል ጸጋ ሰጠን፡” ቁም ነገሩ ይህ ነው። በዚያ ጸጋ መጽናት ከቻልን፡ ጸንተንም እንዲህ ካልን፦ “ይህ ህይወት ካበቃ በኋላ፡ ልንገባበት የምንጠብቀው ሌላኛው ታላቅ አካል ማዶ ላይ እንዳለን እናውቃለን ካልን።” እናም አሁን፡ እነዚህ ሁሉ ውጥረቶች እንደሆኑ—እናሰባቸዋለን።

17 አንዳንድ ሰዎች፡ ክርሰትናን ሲያሰተዋውቋችሁ፡ “እንዲህ ትሆናላችሁ... ከጭንቀት ነጻ ትሆናላችሁ፡” ይሏችኋል። አይደለም፡ ነጻ አትሆኑም። “ከውጥረት ነጻ ትሆናላችሁ።” በፍጹም፡ አትሆኑም! እንደውም ክርሰትያን ሰትሆኑ ውጥረት ይጨምራል፡ ምክንያቱ በጠማማ-አካሄድ ሰትጓዙ፡ ተደሰት-እድልህን-ተጠቀም ነው፡ ሌላው ሁሉ፡ በምታደርጉት ነገር ሁሉ ግድ አይሰጣችሁም።

18 አሁን ግን እውነተኛ ክርሰትያን ከሆናችሁ በኋላ፡ እያንዳንዷ ደቂቃ ታሳሰባችኋለች፡ “ጌታ በእኔ ይደሰት ይሆን? ከሱ መሰማት በቻልኩ!” ውጥረት ውሰጥ ይከታችኋል፡ ጠንቃቃ ያደርጋችኋል። እናንተን እናንተ እንድትሆኑ የሚያደርጋችሁ ይህ ነው። ሰለዚህ፡ ውጥረት በረከት ነው። ችግሩ ግን እይታችሁ ነው። ችግሩ እይታችሁ ነው። እያችሁ? በሌላው ጎኑ ማየት ብትችሉ፡ የሆነ ነገር—የሆነ ነገር... አንድን ነገር ምንም ያህል አድቅቃችሁ ብትከትፉት፡ ሁሌም ሁለት ገጽታ ማግኘታችሁ አይቀሬ ነው፡ እያችሁ። ሰለዚህ ሁለቱ ገጽታዎች መመልከት አለባችሁ።

19 ስለዚህ እኔ ውጥረትን… የማስበው፡ “ኦህ ማይ፡ እንዲህ ነው… ውጥረት ምንድነው? ከዚህ ውጥረት ጋር ባልወለድ ኖሮ።” ይህ ውጥረት፡ ባይኖረኝ ኖሮ’ማ፡ አሁን እኔ እልሆንም ነበር። ምናልባትም፡ ክርስትያን አልሆንም ነበር። ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ያንደረደረኝ ይህ ውጥረት ነው። አያችሁ? ስለዚህ፡ ይህ ነገር ለእኔ በረከት ነበር።

20 እንዲሁም፡ ጳውሎስ ጫና ይሁን ውጥረት በበዛበት ጊዜ፡ እንዳለው፡ ጌታ ከላዩ ላይ እንዲያነሳለት ሶስት ጊዜ—ለመነው። ጌታም “ሳኦል ሆይ፡ ጸጋየ… ጳውሎስ ሆይ፡ ጸጋየ ይበቃሃል፡” አለው።

21 “ከዚያ በኋላ፡ በድካሜ እመካለሁ። ሰደክም ያኔ ብርቱ ነኝ፡” አለ። አያችሁ? በእግዚአብሄር ፈቃድ ብቻ ይሁን እንጂ፡ ሁሉም በጎ ነው።

22 እኔም፡ እጅግ በሚያስፈራኝ፡ እና በሚያስደነግጠኝ ጊዜ፡ ለመንኩት። ሰምንት አሰር ዓመት በፊት ይሆናል፡ እንዲህ ነገረኝ፦ “ከእንግዲህ አያስደነግጥህም፡” አለኝ። ከዚያ ወዲህ አሰደንግጦኝ አያውቅም። በፍጹም፡ ወዳጄ፡ አትጨነቅበት—በፍጹም አትጨነቅ። ሰሜቱ ይሰማኛል፡ እሱ ከጎኔ እንደሆነ ግን አውቃለሁ፡ ከእንግዲህ ስለማያስደነግጠኝ ዝም ብየ ጉዳየን እቀጥላለሁ።

አሁን እሱ፡ “ካሁን በኋላ አትደነግጥም፡” እንዳለ ሁሉ፡ “ካሁን በኋላ አይሆንም፡” ማለት ይችላል።

23 ስለዚህ ይህ መሆኑ የእሱ ፈቃድ ነበር፡ እኔም ተቀብየ እንዲህ አልኩ፡ “ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡ ብየ መንገዴን ቀጠልኩ።”

24 አሁን፡ አንድ አፍታ—ለጸሎት አንገታችን ዝቅ እናድርግ። ልዩ ጸሎት የሚጠይቅ ሰው አለ? (እዚህ የተዘጋጁ መሃረቦች ይታዩኛል።) እጆቻችሁን አንሱ። ጌታ ሆይ፡ ልጆችህ ሁሉ ባርክ።

25 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ አሁን ወደ ታላቁ፡ የጸጋህ ዙፋን ስንቀርብ፡ እንድንመጣ ስለተጠየቅን ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ትዕዛዝ መጥተናልና። እርሱ ስለ እኛ ያሰባልና፡ የሚያሰጨንቀንን ሁሉ ይዘን መጥተን በእርሱ ላይ እንጥላለን። እሱ እንደሚያስብልን ማወቃችን እንዴት ያለ ታላቅ ማጽናኛ ነው። ፈጣሪ፡ ታላቁ የሰማይ አምላክ፡ ለእኛ ለፍጥረቱ፡ ያሰባል። ጌታ ሆይ፡ በዚህም ደስ ይለናል። በምንኖርበት በዚህ ጊዜ መጽናናት ማግኘት የሚቻል፡ ከማይመስልበት—ቃልህ ግን በእውነት ለእኛ መጽናናትን ሆኖናል። ቃል ኪዳንህ፡ መጽናኛችን ነው። በቃል ኪዳንህም፡ የምትሹትን አስታውቁ፡ “በስሜ የምትለምኑት ሁሉ፡ እኔ አደርገዋለሁ፡” ብለሃል። ሌሎች ታላላቅ ቃልኪዳኖችም፡ “ጠይቁ ትቀበላላችሁ። ባትጠራጠሩ፡ እና ይሄን ተራራ፡ ‘ተወርወር፡’ ብትሉት ይወረወራል።” ከነዚህ ሁሉ ቃል ኪዳኖች፡ የምንሻውን ሁሉ ማግኘት እንችላለን።

26 ጌታ ሆይ፡ እጆች ተነስቷል፡ አንዳች ነገር ይጠብቃሉ። አባት ሆይ፡ የሚሹትን አንተ ታውቃለህና፡ ስጣቸው። እኔም አብሬአቸው ጸሎቴን አቀርባለሁ፣ አብሬአቸው እጆቼን አነሥቻለሁ። በዚህም ጠረጴዛ ላይ፡ መሃረቦች እዚሁ ተደርድሯል። አቤት ጌታ ሆይ፡ እንዴት ያለ እምነት ባለው፡ ብርቱ እምነት… ባለው ህዝብ ባርከኸኛል፡ ለታመሙት መጸለይ እንድችል አርገኸኛል።

የትም ይሁን፡ በሁሉ፡ የትም ብሄድ፡ ለታመሙት መጸለይ መቻል ሆኖልኛል። አምላክ ሆይ፡ አሁንም እርዳኝ። እነዚህ ጥያቄዎችን እንድትመልስ በትህትና ሰዎች በነዚህ መሃረቦች ያቀረቡት ጥያቄ፡ እዚህ ተቀምጧል። ምህረትህ በላያቸው ትሁን።

27 ጌታ ሆይ፡ እህት ሂክስ አንዲት ሴት ይዛ መምጣቷን ተረድተናል፡ ካንሰር ስለያዛት፡ እንዲጸለይላት ከርቀት በርራ መጥታለችና፡ እዚህ ልታቀርባት ከቻለች ማወቅ ትፈልጋለች። አምላክ ሆይ፡ የዚያች ሴት ህይወት ትታደግ ዘንድ እጸልያለሁ፡ አድርግልን። ህጻን ሚኪ፡ የወንድሜ ልጅ፡ ታሞ እያስታወከው፡ ከብርቱ ትኩሳት ጋር፡ ከበሩ አለፍ ብሎ እዚያ ተኝቶ ነበር። ጌታ ሆይ፡ እንዲቆምለት አድርገኸዋልና—የእምነት ጸሎት መጸለያችን አምናለሁ፡ በዚህም—እኔ—አንተን አመሰግናለሁ፡ እኔ ክፍሉን ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት ትኩሳቱ ልጁ ለቆ ሄዷልና።

28 አሁን፡ ጌታ ሆይ... ስለሁሉ አመሰግናለሁ። አሁንም ቃልህን ለመናገር ዕጣው በእኔ ላይ ወድቋል። ጌታ ሆይ፡ ቃልህን ሰጠን። "ቃልህ እውነት ነው።" ዛሬ ምሽት ከቃል ኪዳኑ መቅዳት እንድንችል፡ ነፍሳችንን ባርካት—የሚያስፈልገን ጸጋ፡ ከቃልህ ሰጠን፡ ይህም ሳምንቱን እንድንሻገር ይረዳናል፡ አድርግልን። ብርቱ ፓስተራችንን፡ ነፍሱ፡ ሚስቱ፡ ልጆቹ፡ ድያቆናት፡ እና ባለአደራዎችን ሁሉ፡ እና ወደዚህ ህንጻ የገባውና የወጣው የትኛውን ሰው ባርክልን፡ አባት ሆይ፡ አድርግልን። ይሄን በረከት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጠየቅን። አሜን።

29 አሁን፡ ከጌታ ጽሑፎች ከሁለት ቦታዎችን ማንበብ እፈልጋለሁ። መጀመርያ ከመዝሙረ ዳዊት፡ ከ86ኛው አነባለሁ። ከዚያ ቀጥየ ከቅዱስ ማቴዎስ፡ 16ኛው ምዕራፍ፡ ከ 1 እስከ 3። ከመዝሙረ ዳዊት ሙሉውን ሳይሆን፡ ከፍየ አነባለሁ እስከ ቁጥር 11 ድረስ፡ ከግማሽ በላይ ይሆናል።

30 ምናልባትም ከመሰበኬ በፊት፡ የሰብከቴ ርዕስ፡ **የአንድነት ዘመን እና ምልክቱ፡** እንደሆነ ማሳወቅ እፈልጋለሁ። "አንድ የመሆን ጊዜ ምልክት፡" ትንሽ ግራ የሚያጋባ ነገር ይመስላል። **አንድነት** (አያችሁ? ) **ዘመን**፡ ጊዜው አሁን ነው፡ የአንድነት ዘመን ነው። እንዲሁም የሕብረቱ ዘመን **ምልክት**።

31 በመዝሙረ—ዳዊት፡ 86ኛው ምዕራፍ፡ ዳዊት እንዲህ ጸለየ።

> **አቤቱ፥ ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፥ አድምጠኝም፥ ችግረኛና ምስኪን ነኝና።**
>
> **ቅዱስ ነኝና፥ ነፍሴን ጠብቅ፤ አምላኬ ሆይ፥ አንተን** የታመነውን **ባሪያህን አድነው።**
>
> **አቤቱ፥ ቀኑን ሁሉ ወደ አንተ እጮኻለሁና፥ ማረኝ።**
>
> **የባሪያህን ነፍስ ደስ አሰኛት፥ አቤቱ፥ ነፍሴን ወደ አንተ አነሣለሁና።**
>
> **አቤቱ፥ አንተ መሓሪና ይቅር ባይ ነህና፥ ምሕረትህም ለሚጠሩህ ሁሉ ብዙ ነውና።**
>
> **አቤቱ፥ ጸሎቴን አድምጥ፥... የልመናዬንም፥ ድምፅ ስማ።**

**ትመልሰልኛለህና** **በመከራዬ ቀን ወደ አንተ እጠራለሁ።**

“አንተም ትመልሰልኛለህ።” ኦህ፡ ደስ አይልም?

**አቤቱ፥ ከአማልክት የሚመስልህ የለም፥** እንደ ሥራህም **ያለ የለም።**

**ያደረግሃቸው አሕዛብ** ሁሉ **ይመጣሉ፥ አቤቱ በፊትህም ይሰግዳሉ፥** እነርሱም **ስምህንም ያከብራሉ፤**

**አቤቱ፥ ድንቅ የምታደርግ አንተ ታላቅ ነህና፥ አንተም ብቻህን ታላቅ አምላክ ነህና።**

አሁን አድምጡ፡

**አቤቱ፥ መንገድህን ምራኝ፥ በእውነትህ—እሄዳለሁ፤ ስምህን ለመፍራት ልቤን አንድ አርጋት።** (አንድነት! አያችሁ? )… **ስምህን ለመፍራት ልቤን አንድ አርጋት።**

32 አሁን እኔ የማወራበት ርዕስ **አንድነት** እና **ዘመን ምልክት** ነው። አሁን፡ ወደ ቅዱስ ማቴዎስ 16ኛው ምዕራፍ፡

**ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንም ቀርበው፡… ሲፈትኑት፡ ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው** ለመኑት።

እርሱ **ግን መልሶ እንዲህ አላቸው። በመሸ ጊዜ። ሰማዩ ቀልቶአልና** ብራ… **ይሆናል** ትላላችሁ።

**ማለዳም፥ ሰማዩ** ደምኖ… **ቀልቶአልና፥ ዛሬ ይዘንባል ትላላችሁ።** እናንተ **ግብዞች** ሆይ፡ **የሰማዩን ፊትማ መለየት** ታውቃላችሁ፥ **የዘመኑንስ ምልክት መለየት** አትችሉምን?

ጌታ በቃሉ መነበብ ላይ ድንቅ በረከቱ ይጨምርበት።

33 አሁን አንድነትን፡ የአንድነት ዘመን፡ የአንድነት ዘመን ምልክት፡ በተመለከተ እንነጋገራለን። አያችሁ፡ መጨረሻ ላይ ባነበብነው ቃል፡ ኢየሱስ ይታያል፡ ሊቃውንት የሚባሉትን ዘመኑን እና የዘመኑ ምልክትን ባለመለየታቸው ይገስጻቸዋል። አያችሁ፡ ይሄ ነገር፡ ለሰዎች ሁሌ ታላቅ ነገር ነው፡ **የምትኖሩበትን ዘመን ምልክቱ** መለየት መቻል ትልቅ ነገር ነው፡ ማንም ከዚህ እንደማያመልጥ አድርጎ እግዚአብሄር በግልጽ ተናግሮታልና።

34 እስኪ አሁን፡ በፊት ከነበሩ አገልጋዮች፡ አንዳንዶቹን እንዲሁ ላንሳ፡ በመጽሀፍ ቅዱስ ዘመን የጌታ ባርያዎች ከነበሩት አንዳንዶች (በኖህ ዘመን እንደነበረው ምልክት፣ የዳንኤል ዘመን ምልክት እና—የተለያዩ ምልክቶች፡ ወዘተረፈ)፣ ግዜ መቆጠብ—እንድንችል… ለዛሬ እልፈዋለሁ፡ ነገር ግን ይህ የእግዚአብሄር አሰራር ነው፡ ተፈጥሯዊ የዘመን ምልክት ይሰጣቸዋል፡ ይህም—ሰው ሁሉ ምን አይነት ዘመን—እንደሆነ እንዲለይ ነው። ፈሪሳውያኑም ዘመናቸውን መለየት ነበረባቸው። ዘመኑ ምን እንደሆነ ማወቅ ነበረባቸው። በአንዱ ስፍራም፦ “እኔንስ ብታውቁኝ፡ ቀኔን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር፡” ብሏቸዋል። አያችሁ? እኛ—ይህን፡ ማወቃችን—እጅግ ታላቅ ነገር ነው። አያችሁ፡ “አለመረዳት!”

35 ሁሌ ስለ ነብያት ሲናገሩ የሚያነሱት ይህ ነው፡ እንዲህ ይላሉ፦ “ከጌታ በመጣለት ራዕይ፡ ተረዳ። የጌታ ቃልም ወደ ጥንታውያን—ነብያት መጣ ይላሉ።” አያችሁ፡ በነብያት በኩል፡ በጌታ ቃል፡ ይረዱታል። ከዚያ በኋላ፡ ነብያቱም ምልክት ይሰጣሉ። በአንድ ጎኑ ለብዙ ቀናት እንደተኛ፡ ዞሮም በሌላኛው ጎኑ እንደተኛው፡ ዓይነት ሰው ነው። አንዱም ልብሶቹን ቀደደ። አቤት እንደው፡ የመኖራቸው ምልክት ለማሳየት ያደረጓቸው ብዙ ነገሮች አሉ። አሁንም ሰማይ እና ምድርን የፈጠረው አምላክ፡ ጊዜውን በምልክት ለማጽናት—ሰራዎቹን የሰጠው ያው አምላክ፡ ዛሬም ህያው ነው። ስለዚህ፡ እኛም… በምንኖርበት ዘመን—እንደምናየው፡ አንዳች ነገር መኖር አለበት፡ ሰው መረዳት የተሳነው፡ አንዳች ነገር ሳይኖር አይቀርም። አያችሁ? ምክንያቱ የምንረዳበት አንዳች የተረጋገጠ ምልክት ሳይሰጠን፡ እነዚህ ነገሮች፡ በፍጹም—አያደርግም።

36 ቀሳውስቱም፡ በትክክል አላነበብንም እንጂ፡ ዛሬ ያለው ጉዳይም ይህንኑ ነው። ያኔ እንደነበረ ዓይነት ነገር ነው፡ እነሱ ጊዜው እንደሆነ ማስተዋል አልቻሉም። ያኔ—ሰላማዊ ኑሮ የሚኖሩ ይመስላቸው ስለ ነበር፡ መሲሑን አይጠባበቁም ነበር። ኢየሱስም ይሄኛውን አመጣጡ “እንደሌባ በሌሊት ነው” ብሎታል፡ ሰዎች ሁሉ—መምጣቱን በማያውቁበት መንገድ። እሱን ለመገናኘት የወጡ፡ ግማሽ የሚያህሉ ደናግል ግን ነበሩ፡ በመቅረዛቸው ዘይት ሞልተው፡ ያቺ ምልክት ይጠባበቁ ነበር። እኔ ዛሬ የማወራቸው ሰዎችም እነዚያን ነው፡ አያችሁ፡ እነዚህም ምልክቱን፡ የእሱን መምጣት ምልክት የሚጠባበቁ ናቸው።

37 እነዚህ በጌታ የተሰጡ፡ ምልክቶች የተሰጡት፡ ለአማኞች ብቻ ናቸው። የማያምኑቱ አያዩትም። በላዩ ይረማመዳሉ እንጂ፡ ፈጽመው አያዩትም። አሁንም፡ ዛሬ ምሽት በዚህ መድረክ የእግዚአብሄር መልአክ ሊቆም እንደሚችል ያክል፡ እንደው እኔ—እናንተን እንደማያቼ ሁሉ፡ እሱን ማየት እንደሚቻለኝ፡ ወይም ደግሞ እናንተ እሱን ማየት ችላችሁ እንኔ ግን እንደማላየው ሁሉ፡ ወይም እኔ አይቼ እናንተ አለማየታችሁ ያህል ነው። አሁን ይህ ማለት፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ ፍጹም እውነት ነው። ታውቃላችሁ ጳውሎስ ወድቆ… እነሱ እያዩ፡ ከመካከላቸው ግን… አንዳቸውም ብርሃኑን ያየ አልነበረም።

38 ይህ ብርሃን ዮሃንስ በህዝቡ ፊት ቆሞ በነበረ ጊዜም በዚች ቦታ ነበር፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችም፡ ቄሳውስት እና—ፈላስፎች፣ ታላላቅ ሰዎች ጭምር በዳርቻዎቹ ላይ ቆመዋል። ዮሃንስም፡ እራሱ፡ የእግዚአብሄር መንፈስ በእርግብ አምሳል ሲወርድ እና በእሱ ላይ ሲያርፍበት አየሁ ብሎ ምስክርነቱ ሰጥቷል፡ ድምጽም፦ “እኔ የማርፍበት በእርሱም ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው፡” ብሏል። ከዮሃንስ በቀር ግን ያየው ሰው አልነበረም። አያችሁ? ለሱ ብቻ የተመደበ ነበር።

39 ለሰብአ ሰገሎቹ፡ ምልክቱ ምን ያክል ግልጽ እንደነበረ አስተውላችኋል? አዩት፡ አንዳች ነገር ነበራቸው… ዕብራውያን ናቸው። ህንዳውያን ኮኮብ ቆጣሪዎች አይደሉም፡ ዕብራውያን ነበሩ፡ ምክንያቱ የአስትሮኖሚ ትምህርታቸውን ለመጨረስ፡ ወደዚያ አገር ስለ ሄዱ ብቻ ነው። ወደ እየሩሳሌም አቅጣጫ፡ ተመልክተው… ሶስቱ ከዋክብት ማየታቸውን ከተረዱ በኋላ ግን እያንዳንዳቸው፡ የመጡበት ዘር—የትውል-ሐረጋቸው፡ ተመልከተው፡ የካም፣

የሴም፣ እና ያፌት፡ የትውልድ-ሐረግ በነዚያ ከዋክብት አዩ። እነዚያ ሶስት ከዋክብት አንድ መስመር ሲሰሩ፡ መሲሕ በምድር መሆኑ፡ ለእነሱ ምልክት ነበር።

40 ኦህ፡ ማይ! አለመምጣታቸው ነው የሚገርመው፡ "ወዴት አለ? የተወለደው የአይሁድ ንጉስ ወዴት አለ? ኮከቡን ከወደ ምስራቅ አይተን፡ ልንሰግድለት መጥተናል። ወዴት አለ? እግዚአብሄር የዚያን ዘመን ምልክት ስለሰጣቸው፡ የሆነ ቦታ ላይ ህጻኑ መሲሕ ማለትም፡ እግዚአብሄር እና ሰው አንድ የሆኑበት አካል መኖሩን አውቀዋል። እግዚአብሄር እራሱን በሰዎች አካል ውስጥ አንድ ያደረገበት፡ ድንቅ አንድነት! ተደረጉ ከሚባሉት ታላላቅ አንድነቶች ሁሉ፡ እግዚአብሄር ከሰው ጋር ያደረገው አንድነት፡ ዋናው ነው፡ ታላቅነቱን እና አምላክነቱን—ትቶ ድንኳኑን በሰዎች ዘር መካከል ዘረጋ፡ ይዋጃቸው ዘንድ፡ ከእነሱ እንደ አንዱ ሆነ። አንድነት። ምን አመጣ? በሰው እና በእግዚአብሄር መካከል ዘለአለማዊ ሰላምን አመጣ። አቤት ምስጋናችን መብዛቱ።

41 አሁን፡ ሰውን ሁሉ፡ እና ኮኮብ ቆጥሪዎቹን ሁሉ አስቧቸው... የተሰጠ ምልክት አልነበረም፡ በወቅቱ፡ የሰዎች ሰዓት ኣቆጣጠር፡ ከዋክብት ናቸው። ወደ ግንቡ ጫፍ ማማ ላይ—የሚወጣ ጉበኛ ይኖራል፡ እሱም ወደ ላይ ወጥቶ ያያል። እና የተለመዱ ከዋክብት በአንድ የተለመደ ኮንስታሌሽን፡ ሲወጡ ካየ፡ ሰንት ሰዓት እንደሆነ ያውቃል። በቅዱስ ቃል "ጉበኛ ሆይ፡ ሌሉቱ ምን ያህል ነው?" የሚለውን ታስታውሳላችሁ፡ ጉበኛውም መጥቶ ክፍለ ጊዜውን ነገረው። አያችሁ፡ ጊዜን በከዋክብት ያውቃሉ።

42 እስኪ አሁን፡ ከዋክብቶቹ ለነዚህ ሶስት ሰዎች ብቻ በትክክል መስመር መስራታቸው ለሌሎች ግን አለመታየታቸው አይገርምምን? አያችሁ? በትክክለኛ መስመር ላይ። እናንተም፡ ከቃል ጋር በትክክል ልትሰለፉ ትችላላችሁ። አያችሁ? እነዚህ ከዋክብት አንድ ሲሆኑ፡ በዚህኛው ኮንስታሌሽን እራሳቸውን አንድ ባደረጉ ጊዜ፡ በተመሳሳይ ጊዜ ሶስት ሰዎች አንድነት አደረጉ። ስለዚህ እነዚህ ነገሮች እውነት እስኪሆኑ ድረስ፡ ከእግዚአብሄር ጋር፡ በቃሉ አንድ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ የዘመኑን ምልክት! አይታችሁት እውነት መሆኑ ልታውቁ ትችላላችሁ። ተረዳችሁት? "ተው ባክህ፡ የማይረባ!" ብላችሁ፡ ልታጣጥሉት ትችላላችሁ፡

43 **ለእናንተ** ግን የማይረባ አይደለም። እናንተ፡ ከቃል ጋር አንድ ሆናችኋል፡ እሱም ይሄው ነው። ያኔ—ወንድም ፓት ሆይ፡ ፍጹም ብርሃን ይሆናል፡ ይህ—ምልክት—ከአማኞች—ጋር አንድ ሆኖ ባየኸው ጊዜ ብሩህ ነው። እኔ የምናገራቸውም እነሱን፡ አማኞቹን ነው፡ የማያምኑት'ማ ፈጽመው አያይቱም። እና ዛሬ በምድር ላይ ቢኖር፡ ይህን ምልክት ማንበብ ለማይችሉ ለብዙ ቀሳውስቶቻችን ዛሬ፡ እንዴት ያለ ተግሣጽ ይሆን ነበር፡ እኛ በዚህ ቤተክርስትያን በየእለቱ የምናነባቸው ምልክቶች፡ እና የምናያቸው ነገሮች። ሌሎችም ያነቡታል የግድግዳውን የእጅ ጽህፈትም አይተዋል፡ ይሁን እንጂ ብዙዎች ይቃወሙታል፡ ፈጽመውም አይመለከቱትም። ምንም ትርጉም አይሰጣቸውም፡ አያስተውሉትም።

44 አሁን አስተውሉት፡ በዚያ ሁኔታ ውስጥ፡ አገር አቀፍ የሆነ ምልክት—አሳይቷቸዋል። ማለት፡ ምልክት እንፈልጋለን፡ ብለው በጠየቁት ጊዜ፡ የተፈጸመ

ምልክት ሰጣቸው። እነሱ ግን የዓለም መጨረሻ መቼ እንደሚሆን፡ እና ምልክቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ ፈለጉ። እሱም ከቅዱስ ቃል በተለያየ ሰፍራ አገር አቀፍ ምልክት፡ እና በሰማያት የሚሆን ሰማያዊ ምልክት፡ እና ምድራዊ ምልክት ጠቀሰላቸው፡ ምልክት፡ በምልክት ላይ፡ ምልክት ሰጣቸው፡ ምልክት ደጋገመላቸው። እና በአንዱ ሰፍራ ላይ... አገር አቀፍ ስለ ሆነ ምልክት ነገራቸው። "አገሮች ሁሉ፡" ባያችኋቸው ጊዜ፡ ይሄን ስታዩ፡ "በኢየሩሳሌም እና ዙርያዋ መሰብሰባቸውን፡" ባሁ ጊዜ፡ የመከራቸው ጊዜ እንደደረሰ እናውቃለን፡ "ኢየሩሳሌም በሠራዊት ተከባ ስታዩ።"

45 ይሄን ከማድረጋቸው፡ በፊት ግን፡ ዓለም አንድ መሆን ነበረባት። እግዚአብሄርም... የሮም ጀነገራል የነበረው፡ ታይተስ፡ ሰራዊቱን አንድ አርጎ መጣ፡ ይህም የዘመኑ ምልክት የነበረውን ከእግዚአብሄር-የተሰጣቸው ምልክት በመቃወማቸው ነው። ታይተስም ከተማዋን ለመያዝ ሰራዊቱ አንድ አርጎ ያዘመተባትም ያኔ ነው። ከዚህ ሁሉ በፊት ግን (የአምላክ ልጆች-ተብየዎቹ) የእግዚአብሄርን ቃል በመቃወም አንድነት ላይ ይደርሳሉ፣ አሰቀድሞ የእግዚአብሄር ህዝብ ለመቃውወም ትውልዱ አንድ ይሆናል። ያንን—ያንን—ያንን ሕብረት፡ አንድነቱ፡ አንድ ላይ ማበራቸውን፡ አያችሁት።

46 እየኖርን ያለነው በታላቁ የአንድነት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ አምናለሁ። እነዚህን ቀይ መብራቶች፣ እና የፍላሽ ሲግናሎች እና ሁሉ (ሴቶች፡ እና ሁኔታቸው፣ ወንዶች፡ እና ሁኔታቸው፣ ቤተክርሰትያን፡ እና ሁኔታዋ ወሰጄ)፣ በሙሉ ልቤ፡ ለዚህች ታናሽ መንጋ ሳሳያት፡ እኛ እንደ እግዚአብሄር ቃል አሰላለፍ ጌታ ኢየሱስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት፡ በዚህ በታላቁ ትንቢታዊው ዘመን፡ አንድነታዊ ሕብረት በማድረግ እና በመዘጋጀት መሰለፋችንን አምኛለሁ።

47 አሁን አያችሁ፡ ቲቶ መጥቶ፡ አህዛብን ሁሉ አንድ ከማድረጉ... ሰራዊቱን ሁሉ ከማዝመቱ በፊት፡ እሰራኤላውያን አንድ ላይ ሆነው ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን እንዳያምኑ፡ ራሳቸውን ለማውገዝ ተባበሩ። ተቃወሙት፡ ወደ ውጭ አውጥተው፡ ሰቀሉት። ሰለዚህ፡ የተላከላቸውን መዳን ቸል ባሉ ጊዜ፡ ይሄን ለመፈጸም አንድ ሆኑ። አሁን፡ ይሄን ያዙልኝ፡ የዘመኑን መልዕክት ለመቃወም! የሕብረት አንድነት አደረጉ፡ ይህ እንዲሆን ግድ ነበር። ይሄን ካደረጉ በኋላ፡ ወድያውኑ አገር አቀፉ ምልክት ታየ።

48 ሌሎች ህዝቦችም ህብረት ማድረግ ጀመሩ፡ ቲቶም ይህን ታላቅ ሠራዊት የሮማውያንና የግሪክ ሰዎችን አምጥቶ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ከበበ፡ በውስጧ የሚኖር ህዝብ ሁሉ ከበባ ውስጥ አሰገባ፡ እሰከ ሞት ድረሰም ተራቡ። የታሪክ ሊቅ፡ ጆሲፈስ፡ የዛፍ ልጥ ተመገቡ። የምድር ሳርም በሉ። በማለት ያሰረዳል። ሌላው ቀርቶ አንዱ የሌላው ልጆች ቀቅለው በሉ፡ እብዶች እንደነበሩ ተመልከት። በመጨረሻም፡ ቲቶ፡ በኢየሩሳሌም ዙሪያ፣ ወደ ኮረብታው፡ ሲደርሰ፣ በዘመቻ የሚገባውን ሰራዊት በተመለከቱ ጊዜ፡ ህዝቡ ሁሉ—የእግዚአብሄር ፈቃድ የሚያደርጉ ይመሰላቸው ነበር። ታላቁ መምህር፡ ጌታ ኢየሱስ የነገራቸውን ነገር፡ አንሰማህም አሉት።

49 በመካከላቸው የቀረ አንድም ክርሰትያን አልነበረም፡ ምልክቱን አይተው ወጥተዋል። አያችሁ? እንዲህ ተብለዋልና፦ "በዚያም ቀን በሰገነት ያለ ወደ ቤቱ አይውረድ፡ በእርሻ ያለውም፡ ልብሱን ይወሰድ ዘንድ ወደ ኋላው

አይመለስ፡ ወደ ይሁዳ ግን ሽሹ፡ ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ።" ምክንያቱ፡ በክረምት ጊዜ፡ ተራሮቹ ሁሉ—በረዶ ስለሚሞሉ፡ በሰንበት ደግሞ፡ በር—በሮች፡ ደጆቹ ስለሚዘጉ፡ በዚያ ሁኔታ ይያዛሉና። አያችሁ? ጌታ ቢፈቅድ፡ በቅርብ ጊዜ... እግዚአብሄር እነዚህን ነገሮች፡ እንዴት እንደሚሰራቸው እናያለን።

50 አስተውሉ አሁን፡ እሱ... ኢየሱስ ጸልዩበት ሰላላቸው፡ እንዲህ እንዲሆንላቸው ጸለዩ... እንዳይደርስባቸው ጸለዩ፣ እንዳቸውም በዚያ ነገር አልተያዙም። ምልክቱን ሰላዩ ሄደዋል፡ ሰለ እነርሱ ያለው መረጃ፡ መሄዳቸው ነው።

51 አቤት፡ ዛሬ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የምንኖርበትን ዘመን ምልክት እንዴት ማየት አለባቸው! ሰለ ሕይወትህ፡ እቅምህን የፈቀደውን ያህል ወደ ቀራንዮ አምልጥ፡ ወደ ቤተክርስትያን ሳይሆን፡ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሽሽ። ከእርሱ ጋር አንድነት አድርግ፡ ከድርጅቶች ወይም በቤተክርስትያን መመርያ አትጠመድ። ከክርስቶስ ጋር አንድ ሁን፡ እሱ መሆኑንም እርግጠኛ ሁን። ካገኘኸው ጋር መሆን የለብህም፡ ሰለ'ሱ እርግጠኛ መሆንህ ግድ ነው። እንዴት ያለ የአንድነት ዘመን ነው!

52 አሁን፣ መሲሑን እንዳልተቀበሉና ራሳቸውን አንድ እንዳደረጉ ደርሰንበታል እና የራሳቸው ሊግ መሰርተዋል ከዚያም አልፎ—አንድ... ሕግ አርቅቀዋል፡ ኢየሱስን እንደ ነብዪ የሚቀበል የትኛውም ሰው፡ ከቤተክርስትያን እንዲወገዝ ወሰኑ። እዉር ሆኖ የተወለደውን ሰውየ ታስታውሱታላችሁ? ደቀ መዝሙር እንዲህ ብለው ነበር፦ "ሐጥያት የሰራው ማን ነው? እሱ፣ ወይስ አባቱ፣ ወይስ እናቱ? "

53 ኢየሱስም "በሱ ጉዳይ ላይ፡ ማናቸውም አልሰሩም፡ የእግዚአብሄር ክብር በሱ ይገለጥ፡ ዘንድ ነው እንጂ፡" አላቸው።

54 እናት እና አባቱ እንዳች መመስከር እንዳልቻሉ፡ ታስታውሳላችሁ። "ልጃችን እንደሆነ እናውቃለን፡ ማን እንደፈወሰው ግን እኛ አናውቅም፡" አሉ። ነብዪ ነው ብሎ ስለሱ የሚመሰክር ሰው፡ እንዲወገዝ አይሁዶች ተናግረው ነበርና።

55 አያችሁ፡ የእግዚአብሄር ሰራ ግን፡ ይህ ሰው የድርጅቶች አባል ሆኖ እንዳይቀር ነበር። እሱም ሲናገር፦ "እንግዲህ ይህ ሰው ከየት እንደመጣ አለማወቃችሁ ይገርመኛል፡ እሱ ግን አይኔን ከፍቶልኛል።" አያችሁ? አያችሁት አሁን፡ ለመናገር ደፈረ። የእግዚአብሄር ሰራ ማለት፡ እንዲህ ነው። ተፈውሰዋል፡ ጤነኛ ሆኗል፡ ስለዚህ ከምንም ጋር የተሳሰረ ነገር ስለሌለው—ለመናገር ችሏል። ድርጊቱ የተፈጸመበት አካል እሱ ራሱ ሆኖ፡ በርግጥም በህይወቱ ለመጀመርያ ጊዜ... ይህንን አይቷል።

56 እና አይሁዶች፡ ጸረ ኢየሱስ—ጸረ መሲሓዊነቱ፡ እና ጸረ መሲሐዊ መልዕክቶቹ ለመነሳት አንድነት አደረጉ። አሁንም ተመሳሳይ ነገር ሲፈጸም፡ አንድ አይነት ነገር ሲፈጸም አይተናል። ኮሚኒዝም ቤተክርስትያንን ለማጥፋት አንድ ሆኗል፡ ይህ የሚሆንበት ብቸኛው መንገድ ግን... ቤተክርስትያንም አንድነት ካደረገች በኋላ ነው፡ መልዕክቱን ለመካድ እና ቃሉን፡ ለማፍረስ፡ ከአብያተ ክርስትያናት ጉባኤ፡ ከዓለም የአብያተ ክርስትያናት ጉባኤ ጋር ሕብረት ካደረገች በኋላ ነው! እንፈልግህም ብለውታል፡ ቤተክርስትያን

ቃሉን ተቃውማዋለች! ከሐይማኖት ተቋማቸው መመርያ ጋር ስለሚቃረንባቸው ሊቀበሉት አይቻላቸውም፡ ምን ያህል የእሳት አምድ—በህዝቡ መሃል ይቁም፣ ወይም ምን ያህል ሰዎች... የተነገረላቸው ቢፈጸም፣ በመጨረሻ ዘመን ይሆናሉ ያላቸው ምልክቶች በመካከላቸው ቢፈጸሙም እንኳ፡ አይቀበሉትም።

57 ስለዚህ፡ አሁን ራሳቸውን አንድ እያደረጉ ነው፡ ፓስተራችሁ እና እዚህ ያሉ ብዙዎች ሊነግሯችሁ ይችላሉ፡ እየተነበበ፡ በዓለም—የኢኩሜኒካል—እንቅስቃሴ... ውስጥ መሆናቸው የሚነበብ ነው። የሉተራን አገልጋዮችም... በውስጧ አሉ። ምናልባት፡ አደጋ ቢያጋጥም፡ በዚህ ሰፈር ችግር ቢፈጠር፡ በዚህ የኢኩሜኒካል እንቅስቃሴ ውስጥ ያልተካተትን ከሆንን፡ ቤተክርስትያናችን እንደ ቤተክርስትያን አትታሰብም፡ እንደ ዕቃ ክፍል ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ወይም አንድ ሰው ሲሞት ወይም ሲጎዳ አይተን፡ እንዳችን መንፈሳዊ በረከት ልናገለግላቸው ብንሞክር፡ ልንገደል እንችላለን፡ በትክክል። ምንም ነገር ብናገለግል ወደ ፌደራል ማረሚያ ቤት ለአስር ዓመታት ልንወረወር እንችላለን፡ ምክንያቱም የኢኩሜኒካል እንቅስቃሴ አባል ባለመሆናችን ብቻ። የአውሬው ምልክት አይታያችሁምን? አያችሁ? አያችሁ?

58 አሁን፡ ይህ የአንድነት ዘመን ሲመጣ ይታየናል። አያችሁ? አሁን፡ ተመልከቱ! ቤተክርስትያን እራሷን ጸረ መልዕክቱ አንድነት ትፈጥራለች፡ ይሄን ስታደርግ፡ አሕዛብ እሷን ለማጥፋት እራሳቸውን ከኮሚኒዝም ሰር አንድነት እየሰሩ ይገኛሉ፡ ያኔ መጀመርያ እንደሆነ ዓይነት። ዳግም እራሱን ደገመ።

59 እስራኤል መጀመሪያ መልእክቱን መቃወም ነበረባቸው። መልዕክቱን በተቃወሙት ጊዜ፡ (የሌሎች ህዝቦች)፡ ሠራዊት፡ እና አገር አቀፍ ህይወት አንድ ይሆናሉ፡ መጥተውም ቤተክርስትያኒቱን ያጠፏታል። ስለዚህ ዛሬ፡ የጌታ ኢየሱስ መልዕክት ተቃውመውታል፡ እንፈልግም ብለው አዋርደውታል። ስለዚህ አሁን፡ ጸረ ቤተክርስትያን ለመሆን ኮሚኒዝም ዓለምን ወደ አንድነት እያመጣት ይገኛል። አያችሁ፡ በዚህ መልኩ ሊሆን ግድ ነው። አሁን ግን፡ ለመናገርም ይከብዳል።

60 ለእነዚያ አይሁዶች ይሄን ለማመን ከባድ ነበረ። እንዲህ አሉ፦ “ወንድሞች ሆይ፡ አሁን ኑና፡ አምላካችን—ከእኛ ጋር እንዳለ—አይተነዋል፡ ስለዚህ—ወደ ቤተ መቅደስ እንግባ። እንጸልያለን፡ ብጹእ አባታችን **እከሌ-እና-እከሌ** እንዲሁም ብጹእ አባታችን **እከሌ-እና-እከሌ** በጸሎት ይመሩናል። ደጁን ዝጉ!” ቲቶም ውሳኔውን አስተላልፏል፡ አንድ አመት እና ከዚያ በላይ በዚያ ቆይቷል። ዘብ ሆኖ ዘግቷቸዋል፡ እንዲራቡም አድርጓቸዋል፡ አያችሁ። ከከተማዋ መውጣት የሚችል አንድም አልነበረም፡ በረሃብ፡ እየረገፉ ነበር። ግንቦቿን ደርምሶ በገባ ጊዜም፡ በውስጧ የተገኘውን ሁሉ አርዶ ስለነበረ ደም እንደ ወንዝ እንዲወርድ ሆነ።

61 በብሉይ ኪዳን ላይ፡ የእግዚአብሄር መልአክ፡ ይህ እንደሚፈጸም፡ ትንቢት ተናግሮ ነበር። ካህናት የነበሩ፡ ይሄንን ነገር ለህዝቡ ለመንገር የተሾሙት፡ አገልጋዮች፡ ይህን ከማድረግ ፈንታ፡ ኢየሱስ በመካከላቸው በተገኘ ጊዜ፡ ሊያውቁት እንኳን አልቻሉም፡ በአንጻሩ ግን እ—እ... እንዳንድ—ነገሮች ሙከራ-አደረጉ፡ “እስኪ ዘዴውን አሳየን፡ እንዴት—እንዴት እንደሚደረግ አሳየን! ምልክት አሳየን።” አያችሁ?

እሱም አለ፦ “እኔ... ” እንደውም፡ ብዙ ነገሮችን አድርጓል፡ ቢሆንም ሊያዩት አልቻሉም። አያችሁ? የራሳቸው እንደመሆኑ እሱን... የዚያ ዘመን መልዕክት በተቃወሙ ግዜ፡ የዘመናቸውን መልዕክት ተቃወሙ።

62 የዚያን ዘመን ምልክት ማየት ተሳናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ የትንቢት ምልክት—በፊታቸው ተፈጸመ፡ እነርሱ ግን፦ “አሁን እንግባ አሉ!” ቅዱሳን የነበሩ ሰዎች ናቸው። ህይወታቸው ላይ ጣታችሁን የማትቀስሩባቸው ሰዎች ነበሩ። አ—አ—አ ካህን **ሆኖ**፡ የነውር ነገር—ሊኖረው አይችልምና። ካህን የሚፈጽማት ትንሽ ጥፋት፡ በድንጋይ ታሰወግረዋለች ይገደላል። ስለዚህ በንጽህና፡ እና በቅድስና መኖር ይጠበቅበታል። ምክንያቱ በምንም ምክንያት ሊወገር ስለሚችል፡ ምንም አያደርግም። ስለዚህ አሁን በሰዎች ፊት፡ ቅዱሳን እና ታላላቅ ሰዎች ነበሩ፡ ገብተው ግን እንዲህ አሉ፦ “አሁን፡ እንዲህ እናደርጋለን... እኛ አምላክ አለን፡ አምላካችንም በዘመናት ሁሉ ከእኛ ጋር ያለው አምላክ ነው። ወደ ቅዱስ መቅደሱ እንገባለን።” ቤቱ የእግዚአብሄር ቅዱስ መቅደስ ነበር! ነገር ግን፡ አያችሁ፡ በገዛ ቤተ መቅደሱ ተካደ። አያችሁ? “ወደ ጌታ ቤት እንግባ። ሁላችሁም እብራውያን እንደምታውቁት፡ እኛ እዚህ ያለነው፡ የተመረጠ ዘር ነን። እግዚአብሄርም አምላካችን ነው፡ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ፣ እና የያዕቆብ። እሱ ከእኛ ጋር ነው። (እንደ ቀድሞ ዘመን)፡ አሁንም ካልተገረዙት ፍልስጥኤማውያን፣ ከእነዚህ ሮማውያን እና ግሪካውያን ይታደገናል። ወደ ጌታ ቤት እንሂድ! እሱ ከዚህ ሁሉ ይታደገናል።”

63 ጥሩ ነው፡ ነገር ግን የፈጸሙት በደልስ? የቤቱ አናጺ እንደ ትሁት የገሊላ ሰው ጠራቢ መሰሎ በመካከላቸው ነበር፡ እነሱ ግን ተቃወሙት፡ እግዚአብሄር እራሱ፡ የዘመኑ መልዕክተኛየ እና አካሌ ነው፡ ብሎ መሰክሮለታል። እነርሱ ግን ተቃወሙት። ስለዚህ ጸሎታቸው ሁሉ፡ ትሕትናቸው ሁሉ፡ መሰዋዕቶቻቸው ሁሉ ለእግዚአብሄር ምንም አይደለም። እነርሱም ፈጸሙት! እግዚአብሄርም ሊያጠፋቸው ታላቁ ሰራዊት አንድ አደረገ።

64 ዛሬም እንደ ቤተ ክርስቲያናት በየቤተ እምነት ተቋማት እና በመሳሰሉት፡ የእግዚአብሔርን ቃል ሲቃወሙ እናያለን። ሳይንስ ሳይቀር በፎቶ እና በሌላ ነገር ማረጋገጥ የቻላቸው ነገሮች፡ እነርሱ ግን እንድትነግራቸው እንኳን አይፈልጉም፡ እስከ አሁን ድረስም ሊቀበሉት አይወዱም። ስለዚህ መጽሀፍ ቅዱስ ይሆናል ያለው፡ ቲቶ እንደፈጸመው፡ ይሄን ለማጥፋትም ኮሚኒዝም እየተሰራ ይገኛል። በትክክል!

65 የት እየኖርን እንዳለን፡ አሁንስ አያችሁት? በአንድነት ዘመን ላይ፡ እነዚህ ነገሮች አንድ ሆነው አይተናል። አረ፡ እንዴት ነው እነዚህን ነገሮች ማየት የሚሳነን? በቅዱስ ቃል—እዚሁ ላይ አይታችሁ የተሰፋውን ቃል የት እንደተሰጠ፡ ምን እና ምን እንደሚያደርግ ማየት ትችላላችሁ። አሁን'ኮ፡ ሲፈጸም አይተነዋል። አደርጋለሁ ብሎ ቃል የገባውን በቤተክርስትያን አይተነዋል፡ ሲፈጸም አይተናል። አገራት አንድነት ሲያደርጉ አይተናል። ኢዝሞች አንድ ሲሆኑ አይተናል። አብያተ ክርስትያናት አንድነት ሲፈጥሩ አይተናል። የአንድነት ዘመን ነው። የሕብረት ሰዓት ነው። የዚህ ትውልድ መንፈስ “አንድ መሆን አለብን፡” ነው። የምታወሩት ነገር ሳይቀር መደራጀት አለበት፡ ካልሆነ መንግስትም አይቀበለውም።

66 እኔ—እኔ... እንደ ዜጋ፡ እንደ ዜጋ... እንደ ዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ፡ ይህንን ማድረግ እንደማልችል፡ ታውቃላችሁ፡ የአምስት ዶላር ቼክ ብትሰጡኝ ስሜን እንድጽፍበት እንደማልደፍር። አይይ። አያችሁ፡ አልችልም። አያችሁ፡ የአንድነት ዘመን ነው። ይህ ሁሉ በአንድ ዓይነት ህብረት ውስጥ ማለፍ አለበት፡ እና የአውሬውን ምልክት የሚያመጣው አንድነት ይህ ነው። አያችሁ? ዘመኑ የአንድነት ነው፡ ስራውን እየሰራ ያለውን ወደ'ሱ ለመንደርደር ነው። ከተመለከታችሁት፡ በገዛ አይኖቻችሁ ልታዩት ትችላላችሁ። ነገር ሁሉ የሚደራጅበት፡ የአንድነት ዘመን ነው።

67 አይሁድ—አይሁዶች፡ እንደ—መሲሐቸው፡ ጸረ ኢየሱስ ተደራጁ። ስለዚህም፡ የሆነውን አየተነዋል። አሁንም ቤተክርስትያኒቱን ለማጥፋት፡ ኮሚኒዝም በተመሳሳይ መልኩ ሲደራጅ ይታያል፡ ቤተክርስትያን ከዓለም አብያተ ክርስትያናት ህብረት ጋር በመሆን መልዕክቱን፡ የጌታን ቃል ለማጥፋት ከሞከረች በኋላ። ሊያሰወግዱት ይሞክራሉ። የተለያዩ ስለሆኑ ግን፡ ይሄን ማድረግ የሚችሉበት ብቸኛው መንገድ ጉባኤን በመመስረት ነው፡ እዚህ ሜቶዲስት፡ እዚያ ባፕቲስት፡ ሉተራን፡ ትናንሽ ቡድኖች፡ ፕረስቢተርያኖች፡ ቸርች ኦፍ ክራይስት፡ እና የመሳሰሉት። **ይሄኛው ያኛውን** ይቃወመዋል፡ **ይሄኛውም ሌላኛው**ን ስለሚቃወም፡ ምንም ማድረግ አይችሉም፡ ምስራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ ዶክትሪናቸውም እጅግ ይለያያል። አያችሁ፡ አንዳች ነገር አያደርጉም። በአንድ ራስ ጥላ ስር፡ ከተደራጁ ግን፡ ያከናውኑታል። ያኔ ይሆንላቸዋል።

68 ካቶሊኮች፡ ማለት ሮማን ካቶሊክ እጅግ አንድ የሆኑበት መንገድም ይሄው ነው፡ አንድነትም አላቸው፡ አዎን አላቸው... ብዙሃኑ ሮማን ካቶሊኮች ናቸው፡ የግሪኮቹ እና ሌሎች ካቶሊኮች—ያን ያህል እንደ ሮማን ካቶሊክ አይደሉም። በሕብረት የተደራጁ ናቸው፡ አንድ ላይ እንዲጸኑ ያስቻላቸውም ይህ ነው። ምንም ይፈጠር ምን፡ ጳጳሱ የሁሉ ራስ ነው። አያችሁ? ማንም ምንም ይበል፡ "እሱ—ነቀፌታ የሌለው፡ ምስለ'ኔ—እግዚአብሄር ነው፡ አራት ነጥብ፡ እሱ ማለት የእግዚአብሄር ቀኝ ነው፡ በገሃነም ላይ፣ በገነት ላይ፣ እና በሙታን ማቆያ ላይ ስልጣን አለው።" አያችሁ? ስለዚህ **በዚህ** ሁኔታ ምንም መፍትሄ ሊኖር አይችልም፡ ይሁን ያለው ሁሉ፡ መሆን አለበት።

69 አሁን ደግሞ፡ እንደዚሁ፡ ፕሮቴስታንቶች እራሳቸውን ራስ እያደረጉ ይገኛሉ። መጽሀፍ ቅዱስስ ለአውሬውም ምልክት ተደረገለት አላለምን? ምልክት ምንድነው? እንደ ምሳሌው፡ በምሳሌው የተሰራ ነው። ይሄውላችሁ፡ አንድ አይነት ነው። ይህ ምንድነው? የዘመኑ መንፈስ፡ **አንድነት** ስለሆነ፡ እራሳቸውን አንድ ያደርጋሉ።

70 በአንድነት የሚደራጁበት ምክንያት፡ የዘመኑን መልዕክት ለማጥፋት ነው። እንዴት ያጠፉታል? የእግዚአብሄር ቃል ማጥፋትስ እንዴት ይቻላቸዋል? ያኔ በመጀመርያ እንዳደረጉት ባህልን በመጠቀም፡ ተጽዕኖ አልባ፣ ትርጉም አልባ በማስደረግ፣ የእግዚአብሄር ቃል ተጽዕኖ እንዳይፈጥር ይሰራሉ። አያችሁ፡ እንዲህ በማለት፡ "አይይ፡ ይሄ'ኮ... በእውነቱ፡ እንደውም'ኮ፡... ያቺ እምነት አልባ ሴት... ያደረገችውን አይታችኋል... ስሟን ረሳኋት፡ ማን ነበረች። እሷ... ብዙዎቹን ለማስታወስ እየሞከርኩ ነው።

71 እቺ ባለፈው ሚስ. ኔሽን የተባለችው፡ እንደው እሷን አይነት ሌላ በተነሳልን። ወደ ባንኮኒው ሄዳ ውስኪዎቹን ሁሉ የሰባበረች፡ ምስሎቹን እና እዚያ የነበረውን ሁሉ ይወረወረችው እሷ ናት። ምነው ዛሬ እንደሷ ያሉ ሴቶች ተነስተው፡ እንደሷ ያሉ የሴቶች እህቶቻቸው የተሰቀሉ ስዕሎች፡ እና ሌሎች ቀዳድደው ለማረድ በወጡ? ከእንግዲህ ይህ አይኖራቸውም።

72 አሁን፡ ይህች—እንዲህ ብላ የተናገረች፡ የማታምን፡ ሴት ግን፡ “መጽሐፍ ቅዱስ፡ በህዝብ ትምህርት ቤቶች መነበብ ሕገ መንግስታዊ አይደለም፡” ብላ ሌላም የተናገረች ናት።

73 አሁን ደግሞ፡ መቼም አስተውላችሁ ይሆናል፡ የቅዱስ ቃል ምሁራን ነን የሚሉ ሰዎች፡ እንዲህ ለማለት እየሞከሩ ይገኛሉ፦ እንደውም “በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነገሩት አብዛኞቹ ትንቢቶች፡ ውሸት እና በፍጹም ያልተፈጸሙ ናቸው።” ይሄን ሰምታችሁታል አንብባችሁታልም። የማይናገሩት ነገር የለም፡ አያችሁ፡ የቃሉ ተጽዕኖ ለማጥፋት እየሰሩ ናቸው። በሰዎች መመርያ እና ሰው ሰራሽ በሆኑ ነገሮች በመተካት ማጥፋት ከቻሉ፡ ከቃል ይልቅ በዓይኖቻቸው ፊት የተሻለ ይመስላቸዋል፡ ከዚያ በኋላ በገዛ ባህላቸው—ያጠፉታል። የእግዚአብሄር ቃል ለማጥፋት የሚሰሩበት መንገድ፡ በሐይማኖት ተቋም ፖለቲካቸው ነው።

74 አሁን፡ እያንዳንዱ ቤተክርስትያን የራሱ ፖለቲካ አለው። ቸርች ኦፍ ክራይስት የራሳቸው፣ ክርስትያን ቸርች የራሳቸው፣ እና ባፕቲስቶች፣ ሜቶዲስቶች፣ እና ፕረስቢተርያኖች፡ ሁሉም የየራሳቸው የተለያየ ፖለቲካ አላቸው። አሁን፡ ለያይቷቸው ሰለነበረ ከዚያ እየራቁ ይገኛሉ። አያችሁ፡ ከዚህ ቀደም ሊያደርጉት አይችሉም ነበር፡ አሁን ማድረጋቸው ግድ ነው። አያችሁ፡ ዘመኑ የአንድነት ዘመን ነው፡ አሁን ያላቸውን ሁሉ አንድ በማድረግ ምን ይዘው እንደሚወጡ ለማየት ወደ ላይ ይጎትታሉ። አቤት፡ ከፈረሰ ስጋ ዳቦን በመጋገር፣ እና የጣሳን ቆሻሻ፡ አብረው በማድረግ የሚችሉትን ሁሉ፣ አንድ ላይ በመለወስ፡ የበሰበሰ ቲማቲም በላዩ በመጣል፡ ምን እንደሚወጣልህ ለማየት እንደመጠበቅ ነው። እኔ አንዳችም አልፈልግላቸውም። ኖ፡ ሰር! አሰራራቸው ይሄው ነው። አያችሁ፡ የሚመሩት ህዝብ ኢየሱስ ተረት ነው ብሎ የሚያምን ነው፡ ኢየሱስ ተረት ነው ብላ የምታምን ቤተክርስትያንን ነው፡ ሌሎቹ ደግሞ፡ ጥቂቶቻቸው ነብዪ ነበር ብለው ያምናሉ።

75 አንደኛው “የተአምራት ዘመን አልፏል፡” ብሎ ይናገራል።

76 ሌላኛውም “ምናልባት ይሄን ዓይነት ነገር ሊኖር ይችላል፡” ይላል።

77 እና በዚህም ሁሉ፡ መጽሐፍ ይላል፦ “ሁለቱ ካልተስማሙ እንዴት አብረው ይጓዛሉ? ” አያችሁ? ስለዚህ አሁን፡ አንድነታቸው ይሄው ነው። አንድ ታላቅና ብጹዕ አባት ተብዬው ሰው በላያቸው መሾም ማለት፡ ለአውሬውን ምልክት ማስቀመጥ፡ መጽሀፍ ቅዱስ የተናገረው ይሄ ነው። አሁን የሉተራን አገልጋይ የሆነ ሰው፡ ራስ አድርገው ሾመዋል። እንደው፡ እንደምናየው የአንድነት ዘመን ነው። ኮሙኒዝም እና ሌሎችም አንድ እየሆኑ ይገኛሉ፡ አሁን ሁሉ ተመሳሰሏል፡ በዓለም፣ በቤተክርስትያን እና በሌላም ሁሉ፡ አንድነት እየተደረገ ነው።

78 ተፈጥሮን ተመልከቱ። ኦህ፡ ማይ! ተፈጥሮ፡ ተፈጥሮን ደግሞ ብታዩት፡ አንድ አየነት ነገር እያደረገ ነው። ተፈጥሮ የእግዚአብሄር ምልክቶች ካለንደር

ነው። ይሄን ታውቃላችሁ? ኢየሱስ ተፈጥሮን እንዲያዩ ነገራቸው። የባሕር ሞገድ ይተማል፣ እያችሁ፡ ልዩ ልዩ ነገሮች ይሆናሉ፣ በብዙ ስፍራ ርዕደ መሬት ይሆናል፣ አገራዊ መተረማመስ፣ በሰማይ ምልክት፣ በምድርም ምልክት፣ ስለሚመጣው ነገር የሚናገሩ ምልክቶች በሁሉ ይሆናሉ።

79 ደመናውን ተመልከቱ። ደመናዎች የዝናብ ማዕበል ከማድረጋቸው በፊት፡ የሚሆነውን ታውቃላችሁ? እጅግ ብዙ ትናንሽ ደመናዎች፡ አንድ ትልቅ ደመና ይሰራሉ። እንደው፡ ይሔኛው ጥቂት ነፋስ ሰብስቦ ይነፍሳል፣ ሌላኛውም የሚነፍስ ጥቂት ነፋስ ይሰብሰባል፡ አንድ ሆኖው ይነፍሳሉ፡ ከዚያም አውሎ ነፋስ ይሰራሉ። እያችሁ? ማዕበል ከመሰራታቸው በፊት ሕብረት ያደርጋሉ፡ ማበር ይኖርባቸዋል።

80 ዳኪዬ እና ዝይዎች ስፍራቸውን ከመተዋቸው በፊት አንድ ሲሆኑ እዩአቸው። እያችሁ? ሕብረት ያደርጋሉ። ሁሉም አንድ ሆነው፡ ከዚህኛው ኩሬ ወደዛኛው ኩሬ፣ ከዚህም ወደዚያ ሲበሩ ታዩአቸዋላችሁ። ለመብረር ሲዘጋጁ፡ አንድነት ይፈጥራሉ። እያችሁ፡ ተፈጥሮ... ነው፡ እግዚአብሄር ተፈጥሮን ፈጠረ፣ ተፈጥሮም እንደ እግዚአብሄር ዕቅድ ይሰራል። ተፈጥሮ እንደ ሕጉ ሲሰራ፡ ያልተጻፈ የእግዚአብሄር ስርዓት ነው፡ ሕግ ነው።

81 ወደ መቃብር፡ የሚወርድ መቅኔ፡ አለ ብለን በቀብር ስነ ስርዓት እንደምንናገር፡ ጸደይን ጠብቆ በትንሳኤ እንዲወጣ፡ በዛፉ እግር ስር ለመቆየት ይወርዳል። የእግዚአብሄር ስርዓት ነው። ያንን መቅኔ ወደዚያ ውረድ እና ተቀመጥ የሚለው አዛዥ የለም፡ አትጨምቁትም፣ አታልቡትም። እግዚአብሄር ከመደበለት አሰራር ይልቅ የተሻለ መንገድ የለውም። እግዚአብሄር እራሱ የተሻለ አሰርራ አለው። ቅጠሉ ሲረግፍ፡ መቅኔውን ወደታች ወደ መቃብር አውርዶ ይሰውረዋል። ኢዮብ "ቊጣህ እስኪያልፍ በመቃብር ሸሽገኝ፡" እንዳለ። እያችሁ? የእግዚአብሄር ስርዓት ስለሆነ ከውርጭ በፊት፡ ወደ ታች ይወርዳል። ተመልከቷቸው ቅጠሎች አሁን መርገፍ ጀምሯል። ለምን? የተፈጥሮ ስርዓት ነው።

82 ዳክዬዎች፡ ሁሉም፡ በመሪያቸው ዙርያ፡ ጉባኤ ያደርጋሉ። በዚያም በሆነ መንገድ፡ እንዴት እንደሚያደርጉት እኔ አይገባኝም፡ አንዱ ወንድ ዳክዬ ግን ከመካከላቸው መሪ እንደሆነ ያውቃሉ። በዚህ በትንሹ ጓድ፡ ሁሉም በዙርያው ጉባኤ ያደራጃሉ፡ ወድያውም አየር ላይ ይወጣሉ። እሱ'ኮ... ከኩሬው ፈጽሞ ርቆ አያውቅም፡ ነገር ግን ቀጥ ብሎ እስከ ሊዊዝያና እና እስከ ቴክሳስ ድረስ፡ ሩዝ እርሻው ድረስ ይጓዛል። እያችሁ፡ በዚያ አመት የተወለዱበትን ቤታቸው፡ ትተው ከመብረራቸው በፊት፡ በአንድነት ሕብረት ያደርጋሉ። አሜን! ከሚመራቸው ጋር ጉባኤ ያደርጋሉ፡ ይሄው ነው።

83 ችግሩ ያለው፡ ሰው ላይ ነው፡ መሪውን አያውቅም። አዎን፡ ወዳጄ። በሐይማኖት ተቋም ዙርያ ይሰበሰባሉ፣ በቢሾፕ ወይም በአንድ ሰው ዙርያ ይሰበሰባሉ፣ ቃል ውስጥ በሚገኘው መንፈስ ቅዱስ በሆነው መሪ ዙርያ ግን፡ አይሰበሰቡም። እያችሁ? እነሱ የሚሉት፦ "ኦህ፡ ወግ አጥባቂ፡ ቢሉኝስ፡ በማይሆን መድረክ ላይ ብወድቅስ።" ኦህህህህ፡ ይሄው ነው! ትንሹ ዳክዬ፦ "ይህ ሰው ክንፎቹ ሲዘረጋ አይመቸኝም። እኔ እሱን የምከተል አይመስለኝም"

ቢልስ። በብርድ ትሞታታለህ። በረራውን ሲያደርጉ—አብረህ ካልተነሳህ፡ እዚያው ትያዛታለህ። አንድ ያደርግሀል፡ ይሄን የሚያደርገው ተፈጥሮ ራሱ ነው።

84 ዝይዎች አንድ ሆነው፡ ተመሳሳይ ነገር ያደርጋሉ፡ ሁሉም በመሚመራቸው ዙርያ ጉባኤ ይሰበሰባሉ።

85 ንቦች በመንጋ ሲዘምቱ አስተውላችኋል? ንቦች በመንጋ ከመዝመታቸው በፊት፡ ሁሉም በንግስታቸው ዙርያ፡ ሕብረት ያደርጋሉ። ይህ ትክክል ነው። እሷ ወደ ሄደችበት ሁሉ፡ እነሱም ይሄዳሉ። አዎን! ምን ያደርጋሉ? መንጋ ከመሆናቸው በፊት በአንድነት ያብራሉ። ተፈጥሮ ሁሉ፡ አይሳሳትም!

86 አሶች ጸደይ ከማለቁ በፊት በአንድነት ያብራሉ። በውቅያኖስ ውስጥ፡ "ሀምፊይ፡" ብለን የምንጠራቸው፡ ትልልቆቹ... ሳልሞን፡ ታገኛላችሁ። ወቅት ከማለቁ በፊት፡ በዚያ ሲመጡ፡ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ታያላችሁ፡ የንጹሕ ውሃ ዓሣዎች ሆነው ሳሉ፡ በባህር ላይ፡ ጨዋማው ውሃ ውስጥ፡ በብዛት እየጎረፉ ሲመጡ እና ሲጎርፉ ይታያሉ። እዚህ ጋር ደግሞ ወደ መራቢያቸው ወቅት ለመጓዝ፡ ንጹህ ውሃ ወዳለበት በቀጥታ ይወጣሉ። ወደዚያ ወጥተውም፡ በየአራት አመቱ ይራባሉ፡ መራባታቸው እንደፈጸሙም ወድያውኑ ይሞታሉ። ወደ ሞት እየሄዱ እንዳሉ ያውቃሉ፡ ይሁን እንጂ ምንም ብታደርጉ ልታቆሟቸው አትችሉም። እዚያ ሲደርሱ፡ ወደ መሞቻቸው እንደሚገቡ እያወቁ፡ የዓሣ መሰላል እና መሰናክሎች ሁሉ ይዘላሉ። ወደዚያ ከወጡ በኋላ በጉድጓዶች ተራብተው፡ እንደሚሞቱ ያውቁታል፡ የተፈጥሮው ሰርዓት ግን ያስገድዳቸዋል። ከነሱ በኋላም ትናንሾቹ ይፈለፈላሉ፡ እነዚህም የሆነ ነገር ይሰበሰባቸዋል፡ ወጥተው ወደ ውቅያኖሱ ይሄዳሉ። አንድነት ነው! ሕግ ነው። የእግዚአብሄርን ሕግ ማሸነፍ አትችሉም።

87 አገራት—ተፈረካከሱ፡ እኛ አሁን በምናየው ዘመን—እንዲህ መህሆናቸው ግድ ነው። እኛም አገር አቀፍ አለመረጋጋት ሂደት ውስጥ ነን። አገራት ወዳጅነታቸውን ሲፈረካክሱ ይታያል። በየአመቱ፡ **ይሄኛው** አገር ኮሚኒዝም ውጦት እናገኘዋለን፡ **ይሄኛውም** እንዲሁ በኮሙኒዝም ይዋጣል። እዚሁ የእኛ አገርም፡ የኮሙኒዝም ማር ቅብ ሆናለች፡ ወደ ፊት በሙላት ይወርሳታል! እያችሁ፡ ያደርገዋል፡ የሚያስቆመው አይኖርም። ለምን? ቲቶስን ማስቆም ያልተቻለበት በተመሳሳይ ምክንያት ነው። ህዝቡ እግዚአብሄርን እና ቃሉን አንፈልግህም ብለውታል። አዎን፡ ወዳጄ፡ እንዲሁም ይፈጽሙታል፡ እኛም ሂደቱ በአይኖቻችን አይተነዋል።

88 ብዙ ጊዜ፡ ሁለት ሰዓት እፈጃለሁ፡ አሁን ግን፡ ሰላሳ ደቂቃ ያህል ወሰጄባችኋለሁ። እያችሁ? ይሄን ሁሉ ለማስረዳት ግን፡ እየገፋሁ ነኝ። ቤታችሁ ስትገቡ አጥኑት።

89 አስተውሉት፡ አሁን አንድነት እየፈጠሩ ናቸው። "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እውነትህን ነው?" ብትሉኝ፡ በትክክል የሚያደርጉት ይህ ነው፡ ወደ አርማጌዶን ጦርነት እየተመሙ ናቸው። እያችሁ? አሁን አንድነት የሚያድረጉትም ለዚያ ነው። እነዚህ የእነ U.N. እና የሌሎች መኖር ምክንያት ይህ ነው። የምዕራቡ ዓለም ጸረ ምሰራቃዊው ዓለም አንድነት እያደረገ ይገኛል፡ ኮሙኒዝም እና ሌላ ሁሉ፡ በአንድነት እያበረ ነው። ቸርቾች አንድነት እየፈጠሩ ናቸው። ሌላም ሁሉ አንድ የሚሆን ይመስላል። ራሳቸውን ወደ አንድነት፡ አንድ ሲያደረጉ፡ አይተናል።

90 በተጨማሪ፡ ይህን የአገራት ሁሉ አንድነት ሲሆን፡ ምልክቶች፣ አገር አቀፍ ምልክቶች፣ በዚህ ዓለም ላይ ይታየናል፣ ርዕደ መሬት በብዙ ስፍራ፡ ብዙ ነገር አንድ እየሆነ፡ ዓለምን ወደ ህብረት፣ ሰዎችን ሁሉ ወደ ህብረት፣ ቸርቾችን ሁሉ፡ ሌላውን ሁሉ ወደ ህብረት እያመጣቸው ይገኛል። እና ይህ ዓይነት አንድነት በሚሆንበት ወቅት፡ ሌላ ዓይነት አንድነትም እየተፈጸመ ይገኛል። አሜን! አሁን ላሳያችሁ የፈለግኩትም ይህ ነው።

91 እግዚአብሄር ሙሽራይቱን አንድ እያደረጋት ነው። ከምስራቅ እና ከምዕራብ፣ ከሰሜን እና ከደቡብ፣ እየተሰበሰበች ናት። የአንድነት ዘመን አለ፡ እሱም አሁን ይህ ነው። ለምን አንድ ትሆናለች? ለንጥቀት። አሜን! እግዚአብሄር እያዘጋጃት ነው። አዎን ወዳጄ፡ አንድነት! ከምን ጋር ነው አንድ የምትሆነው? ከቃል ጋር! “ሰማይ እና ምድር ያልፋሉ፡ ቃሌ ግን አያልፍም።” የትኛውም የሐይማኖት ተቋም እና ግለ ሰብ ምንም ቢል እራሷን ጌታ ስራዊት እንዲህ ይላል ከሚለው ጋር አንድ በማድረግ ላይ ናት። እራሷን እያዘጋጀች ናት። አንድ በመሆን ላይ ናት። ለምን? ሙሽሪት ስለሆነች። በትክክል። አያችሁ፡ እራሷን ከሙሽራው ጋር አንድ በማድረግ ላይ ናት፡ ሙሽራው ደግሞ ቃል ነው። “በመጀመርያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሄር ነበረ። ቃል ስጋ ሆነ በእኛም መካከል አደረ።”

92 ቤተ ክርስትያን እና ሙሽሪት እና ቃል አብዝተው አንድ እየሆኑ፡ ቃል እራሱ የሙሽራውን ስራ እስኪሰራ ድረስ ይጣመራሉ። አሜን! አይታችሁታል? አንድነት! ከአሁን በኋላ፡ “የቤተክርስትያን አባል አትሁን”፡ **የዚህኛውም** አትሁን፣ ነገር ግን ከሁሉ ሸሽተህ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ተጣበቅ። አያችሁ? የአንድነት ዘመን ነው። እግዚአብሄር፡ በትክክል፡ ሙሽራይቱን እየመለሳት፡ አንድ እያደረጋት ነው። የቃል ኪዳን ቃሎቹን አንድ ያደርጋቸዋል።

93 ሁለተኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች፡ 2ተኛ ምዕራፍ፡ ማለት 5ተኛ ምዕራፍ ሲናገር፦ “በምድር አፈር ውስጥ የተኙ ቅዱሳን ይነቃሉ። እኛም ከእነርሱ ጋር አንድ እንሆናለን (ህያዋን፡ ሞተው ከነበሩት ጋር)፣ ወደዚያ ከመሄዳችን በፊት ህብረት እናደርጋለን፡” ምክንያቱ እኧ ወደዚያ ስትደርስ መጽሐፍ ቅዱስ ሙላት ያገኛልና። አሁን በህይወት ያሉት፡ እራሳቸውን ከቃል ጋር አንድ ያደርጋሉ፡ የሄዱት ግን አስቀደምው ፈጽመውታል፡ ወደዚያ ከመሻገራቸው በፊት አንዲት ታላቅ የህብረት አንድነት በማድረግ፡ ሁሉም አንድ ላይ ይመጣሉ። አሜን!

94 ኮሙኒዝም ይነሳል፡ ሌሎች ነገሮችም ይነሳሉ፡ ቤተክርስትያንም ወደዚያ ማዶ እራሷን አንድ ታደርጋለች፡ ሌሎችም... እሕዛብ ሁሉ ከዓለም አብያተ ክርስትያናት ጉባኤ ጋር፡ ሙሽራይቱ ግን እራሷን ከእግዚአብሄር ቃል ስር አንድ ታደርጋለች። ይሄን ለማድረግ፡ እግዚአብሄር ሰማያዊ ምልክቶችን እና ሌሎች ነገሮችን ልኳል፡ ለምድሪቱ እንዳረገላት፡ ለቤተክርስትያኒቱም እንዲሁ ማረጋገጫ ይሆናታል። አሜን።

95 ጌታ ሆይ፡ የአንድነት ዘመን ነው! አዎን፡ ወዳጄ። ኦህ፡ ማይ! አሁን አስታውሱ፡ አሁን፡ የቃል አንድነት (እንደገና አንድ መሆን)፡ አለ፡ መልሶ ማምጣት “ለቅዱሳን ፈጽሞ የተሰጠውን አንዱን እምነት።” መልሶ ይመጣል! ይህ የሚሆነው ግን በዚህ ዘመን ብቻ ነው። ይህ መሆን የሚችልበት ብቸኛው ጊዜ አሁን ነው። በየትኛውም ስፍራ እንዲህ ተጠቅቶ አያውቅም፡ በሐይማኖት ተቋም

ጊዜያዊ ደስታ ተወሰዱ። አሁን ግን፡ የየትኛውም ሐይማኖት ተቋም ጊዜያዊ ደስታ አይደሉም፣ ምክንያቱ ዘመኑ ከሁሉ ዘር፣ ከሁሉም ቀለም፣ ከሁሉም ሐይማኖታዊ መመርያ የሆኑ ወንዶች እና ሴቶች አንድነት ዘመን ነው፣ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከክርስቶስ በታች ያለው ምንም ነገር ወደ ቃል ይመለሳል።

96 የቤተክርስትያን የአንድነት ዘመን! ኦህ፡ ማይ! በድርጅቶች ምክንያት እዚህ እና እዚያ የወዳደቀውን ቅዱስ ቃል ሁሉ አንድ ለማድረግ፡ ከኒቂያ፡ ከሮም፡ ከመጀመርያዋ ቤተ ክርስትያን ተቋም ከመሰረቷት በኋላ፣ የሉተርን ተቋም አደረጉት፣ የዌስሊን ተቋም አደረጉ፣ ሌሎች አብያተ ክርስትያናት ሁሉ ተቋም አደረጉት። ይሄን በማድረጋቸውም፡ የሐይማኖት መመርያዎችን ለርሳቸው አቆሙ፡ ከዚያ በኋላ ጌታ አንዳች ነገር ቢልክላቸው፡ መቀበል አልቻሉም። ስለዚህም እስከ አሁንም ድረስ፡ የማይቻል ሆኖ ነበር። ጌታ ግን፡ በመጨረሻ ዘመን፡ እንደ ሰጠን ተስፋ "የአባቶችን እምነት ዳግም ለሙሽራይቱ አቃናለሁ ብሏል፡" እሱም ይሚሆነው በዚህ መንገድ ነው፡ ዘመኑም ከዚህ ዘመን ሌላ ሊሆን አይችልም። ተመልከቱ ከሰማይ የሆነ፡ የእሳት አምድ ምልክት በመካከላችን ተገልጧል፡ ከእርሱም ጋር የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ድንቆች እና ምልክቶች። አንዳች ነገር ሲናገረንም፡ ልክ እንደተናገራት ለመሆን ፈጽማ አትወድቅም። አሜን! እንግዲያውስ ምን ላይ እንደቆምን እናውቃለን። የአንድነት ዘመን ላይ!

97 ዓለማት አንድ ሲሆኑ አይተናል፣ ዓለም አንድ ስትሆን አይተናል፣ ኮሙኒዝም አንድ ሲሆን አይተናል፣ አብያተ ክርስትያናት አንድ ሲሆኑ አይተናቸዋል፣ እግዚአብሄርም እሱ እና ቤተክርስትያን አንድ እስኪሆኑ ድረስ፡ እራሱን ከሙሽራይቱ ጋር አንድ ሲያደርግ አይተነዋል። ሃሌሉያ! ልክ እዚያ ጋር እንደሚታይ ፒራሞድ። አዎን! ሁለቱ በአንድነት ሕብረት አደረጉ፡ እግዚአብሄር አንድነት አደረገ! እንዴት? ከመጀመርያዋ ቤተክርስትያን በኋላ፡ የእሳቱ አምድ በፍጹም፡ በሰዎች ዘንድ አልታየም ነበር። አሁን እኛ ዛሬ የምናያቸው ነገሮች፡ ከመጀመርያዋ ቤተክርስትያን በኋላ፡ በፋጹም አልታዩም። ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው ግን እግዚአብሄር በሰባቱ ማሕተም በኩል ለእኛ በሰጠው ምልክት፣ እና ከሰማይ በተላኩልን ሰባት መላእክት፡ እነሱም በሐይማኖት ተቋማት ውስጥ የተበተኑትን ቃላት እንደገና መልሰው፡ መንፈስ ቅዱስን ዳግም ለማምጣት፡ ወደ እግዚአብሄር ቃል አምጥተው ሰበሰቡልን።

98 ኢየሱስም አለ፦ "በእኔ ብትኖሩ ቃሌም በእናንተ ዘንድ ቢኖር፡ ከዚያ የምትሹትን ለምኑ፡ ይደረግላችኋል።" ሙሽራይቱን ዳግም ከቃል ጋር፡ እሱም እግዚአብሄር ጋር አንድ ሆነች። ቤተክርስትያን እና ቃል፡ ቤተክርስትያን እና የሀይማኖት መመርያ ሳይሆን፡ ሙሽራይቱ እና ቃል ዳግም አንድ ሆኑ። ኦህ፡ ማይ! ምን... ምን አቃና? አያችሁ፡ በሉተር ግሩፕ ተበትኖ የነበረውን፡ የመጀመርያዎቹ የጴንጤቆስጤ አባቶች እምነትን። በሉተር በራሱ አይደለም፣ ሉተር አይደለም፣ ዌስሊ አይደለም፣ ወይም እነዚህን ታላላቅ መሰራቾች አይደሉም። እነሱ ከሄዱ በኋላ ግን፡ የተነሳ ቤተ ክርስትያን ነበረች፡ እነዚህ... ያኔ እንዲህ አደረጉ፣ ከዚያ ውስጥ ተቋም መሰረቱ። የሐይማኖት መመርያዎች እና ሌሎች ነገሮች ተቀበሉ፡ ሄደውም ጠፋ። እና ዛሬ ተመልከቷቸው፡ አሁን'ማ ወደ ዓለም አብያተ ክርስትያናት ጉባኤ ገቡ።

99 አሁን፡ እያችሁ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ከዚህ በፊት ያልሆኑ ነገሮች ሲፈጸሙ፡ አሁን አይታችኋል። እያችሁ፡ የእግዚአብሄር ምልክት ነው፡ እነዚህ ሁሉ አንድነቶች የዘመን ምልክት ናቸው። አሁን፡ ይሄን በጥንቃቄ መርምረን እንዳገኘነው እርግጠኛ መሆን አለብን። እውነተኛውን ቃል ስለ ሐይማኖት ተቋም… ጥለውታል፡ ከቃል ይልቅ የተለያዩ ሰዎችን አስተሳሰብ እና ሐይማኖታዊ መመርያን ለመቀበል ጣሉት።

100 የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 10 እንዲህ አለ፦ “የሰባተኛው መልአክ መልእክት።” አሁን አስታውሱ፣ ልክ በሰባቱ መለከቶች፣ እና ሰባቱ መላእክቶች ሰባት መለከት ይነፋሉ። ቀጥለን የምናየው ይሄ ነው። የት እንደሆነ ግን አስታውሱ፣ በተለይ አስረግጦ “የመልአኩ… ” ስለሚል፡ የሰባተኛው መልአክ መለከት አይደለም፡ ነገር ግን “የሠባተኛው መልአክ መልዕክት።” እያችሁ፡ የመለከቱ መልአክ ሳይሆን፡ የመልዕክት መልአክ ነው! እያችሁ፡ ሰባተኛው መልአክ፡ የመለከቱ መልአክ፡ ያ መልአክ መለከቱን ብቻ ነው የሚነፋው። ይሄኛው ግን ሲናገር፡ “በሰባተኛው መልአክ በመልዕክቱ ዘመን፡” እያችሁ፡ የእሱ መልዕክት በተፈጸመ ጊዜ። እያችሁ፡ የቤተ ክርስትያን ዘመን መልዕክት ይህ ነው። በዚህ ዘመን፡ በመለከት ሳይሆን፡ በመልዕክቱ፡ እንዲህ ያደርጋል… እና “(በቃል ውስጥ የተጻፋትን) የእግዚአብሄር ምስጢር ይፈጽማል።”

101 አሁን የምንኖርበትን ቀን ተመልከቱ! ማኅተሞቹን ተመልከቷቸው፣ የተበታተነውን የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት እንደሰበሰበ፣ ሉተር እና የቀሩትን ሁሉ፣ እና ሌሎች ሪፎርመሮች ሁሉ ያልዳሰሱት፡ እሱ መጣና፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቦታ ቦታቸውን አሳየን፡ እያንዳንዱ ሰው ሰፍራ ሰፍራውን፡ ምን ምን እንደሚያደርግ እና ቤተክርስትያን ምን እንደምትሆን፡ እሱ የሚያደርገው፡ እና ቤተክርስትያን የሚገጥማት ምን እንደሆነ፡ እሱ የተዋቸው ነገሮች ሁሉ። እንዲሁም፡ በመጨረሻው ቀናት፡ እኛ ስለነዚህ ነገሮች አንዳች እውቀት ሳይኖረን፡ አንዳንድ የሚፈጸሙ ነገሮች አስቀድሞ ነገረን፡ ጋዜጦች እና ሌሎች የዳሰሷቸው ነገሮች፡ እሱ መጥቶ ገላለጣቸው ምስጢራቶቹን አንዱ ከሌላው ሰበሰባቸው። አሜን! ወንድሜ፡ ይህ እኔን ማርኮኛል! ይሄ፡ ለእኔ፡ ቃሉን አርሞልኛል። አሜን! ሰዎች የሚሉትን፣ የሚያስቡትን—ቢገደኝ ወይም፡ ባይገደኝ፡ በትክክል፡ ለእኔ እውነት ይሄ ነው።

102 ከባቢሎን እንደመጡ እንደ ሰብአ ሰገሎች፦ “የተወለደው የአይሁድ ንጉስ፡ ወዴት ነው? ማለት አለብን፡ አሁንም እሱ፡ በምድር ላይ አለ። እሱን መፈለግ አለብን።” በትክክል። “እነሆ፡ ሙሽራው መጣ! የእኩለ ሌሊት ጩኸት ይሰማኛል!” ማለት እስከምችል ድረስ እጅግ እንደቀረበ አምናለሁ፡ አሜን! ልክ በፍጻሜው ዘመን ነን። ኦህ፡ ማይ፡ እኛ የምንኖርበት ሰአት። አስተውሉ። እያችሁ?

103 እንዴት ያለ ቀን ነው! ይህ ታላቅ የእግዚአብሔር ምሥጢር የተፈጸመበት፡ እኛም የምንኖርበት እንዴት ያለ ጊዜ ነው፤ ምልአተ መለኮት የመጣበት፡ ምንነቱንም የታየበት ዘመን፣ እነዚህ ትንንሽ ኢዝሞች ወጥተው፡ እሱን **እንዲህ** ነው ይሉታል፣ ሌላም መጥቶ **ይሄ** ነው ይለዋል፣ ሌላኛውም **እንዲያ** ያደርገዋል። የእግዚአብሄር መልአክ ከወረደ በኋላ ግን ኢዝሞቻቸውን ሁሉ አወጣና፣ እውነቱን ከውስጡ ፈልቅቆ ሰቦ፡ አቀረበልን። እነሆ፡ በፍጽምናው

ሙላት መጥቶላችኋል፡ ሌላ መንገድ የላችሁም። እነሆ፡ እርሱ ይህ ነው። አያችሁ፡ የእባቡን ዘር የመሳሰሉ፡ በህዝቡ መካከል እጅግ—ምስጢር የነበሩ የተለያዩ ነገሮች ነበሩ። አያችሁት? ምንድነው? እሱ... የምን ምልክት ነው? የአንድነት!

104 በሚልክያስ 4 ምን ተናገረ? እቃናለሁ አለ! የመጀመርያውን የጴንጤቆስጤ እምነት፣ ያንኑ ጴንጤቆስጤ መልዕክት ጋር፡ ወደ ህዝቡ አቃናው፣ ያው የጴንጤቆስጤ ምልክት፣ ያው የጴንጤቆስጤ ምስክር፣ ያው አምላክ ጋር፣ ያው ሐይል፣ ያው ትምህርት፣ ሳውልን በደማስቆ መንገድ በመታው፡ ያንኑ የእሳቱ አምድ ማረጋገጫ ባለበት፡ አንዳች ነገር ሳያስቀር ያኔ በዚያ ዘመን ያደረገውን ተመሳሳይ ስራ አሁንም እያደረገ ዛሬም በመክከላችን አለ። አንድነት እያደረገ!

105 ህዝቦች አንድ ሲሆኑ አይተናል፣ ዓለም አንድ ስትሆን አይተናል፣ አብያተ ክርስትያናት አንድ ሲሆኑ አይተናቸዋል። ሙሽራይቱ አንድ ስትሆን፡ ከቃል ጋር አንድ ስትሆን አየን። ለምን? ቃል እራሱ እግዚአብሄር ስለሆነ። ቃልም... ሙሽራውም (ቃል እንደመሆኑ መጠን)፣ ሙሽራይቱም (የቃሉን ስሚ ስለሆነች)፣ ወደ ሕብረት አንድነት መጡ። ሁለቱ የአንድነት ሕብረት ጋብቻ ፈጸሙ። አያችሁ፡ ለመጋባት ዝግጅት ላይ ናቸው፣ ከዚያ—አንድ ይሆናሉ። ቃሉ አንተ ይሆናል፡ አንተም ቃሉን ትሆናለህ። ኢየሱስም ሲናገር፦ “የአብ የሆነ ሁሉ፡ የእኔ፣ የእኔ የሆነ ሁሉ፡ የእናንተ፣ የእናንተ የሆነ ሁሉ፡ የእኔ እንደሆነ፡ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ። እኔ በአባቴ እንዳለሁ፡ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፡ እኔም በእናንተ እንዳለሁ፡ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ።” አያችሁ? በዚያች “ቀን።” የትኛይቱ ቀን? ይህች ቀን! ታላቅ እና የተሰወረ የእግዚአብሄር ምስጢራት የተገለጠባት። አቤት፡ ሰወዳት!

106 አቤት፡ ቃል እና ሳይንስ፡ ዛሬ እንዳደረጉት፡ እንደማይነጻጸሩ ተመልከቱ። ከዚህ በፊት አይችሉም ነበር። ማድረግ የቻሉት አሁን ነው።

107 የተናገረውን፡ አስትውሉ፡ “በሰማይ ምልክት፣ በሰማይ ላይ ምልክት።” አሁን ሳይንስ፣ አገር አቀፋዊ ምልክት፡ ዛሬ ዛሬ በሰማይ ላይ ታላላቅ ምልክቶች፣ ብዙ ጠፈርተኞች እና ሌላ ሁሉ አላቸው። ጠፈርተኞቹ፡ ለአለም ምን ምልክት ያመጣሉ? ፍርሃት ብቻ ያመጣባቸዋል። እንደዚያ ያለ ነገር መቼ እንደሚልኩብን እና ቦምቦችን መቼ ጥለውብን፡ እንደምንጠፋ እናውቀውም። አያችሁ? እነሱ በሰማይ የያዟቸው ምልክቶች፡ እጅግ የሚያስፈሩ ትዕይንቶች ናቸው። አያችሁ? አቶሚክ ሚሳይሎች እና ሌሎች፣ ብዙ ዓይነት ምልክቶች፡ አሏቸው።

108 በቀደምለት—የተፈራረሟቸው ስምምነቶች፡ ተመልከቱ፡ ከእንግዲህ ወዲህ በተገለጠው ሰማይ ላይ እንዳያፈነዱ፡ በተመሳሳይ መንገድ ግን ሙከራዎቻቸው፡ ከምድር በታች እና በውኆች ላይ ለማድረግ ነው። አያችሁ? የስምምነት ውል ተፈራርመዋል፡ “እናንተ ይህ አናደርግም ካላችሁ፡ እኛም አንተኲሰም (ነገር ግን ወደ አገራችን ተመልሰን በዚህ መልኩ እናደርገዋለን፡ እናንተም በአገራችሁ ይህን እንደምታደርጉ እንውቃለን)።” አያችሁ? ቁም ነገር የለውም፡ ተራ ነው... መተማመን የለም፡ ምንም ነገር—ምንም ነገር የለም።

እንደው… ማየት ከቻላችሁ? አንዱ ሌላውን እጅግ ተፈራርተዋል። አስፈሪ ምልክት ማለት ይህ ነው።

109 ሳይንስ እና ሰው እና አሕዛብ ሁሉ በሰማይ ላይ የሚያስፈራ ምልክትን አድርጓል። ይህ ትክክለኛ ነገር ነው። አሁን፡ አንዱ አንዳቸውን ተፈራርተዋል። የተሰጣቸው ሰማያዊ ምልክት አለ… አሁን ተመልከቱ፡ እነሱም ሰማይ ላይ የያዙት ምልክት አለ፡ እጅግ አስፈሪ ምልክት ይዘዋል፡ ሰው ጠፈር ላይ ወጥቷል፡ አቶሚክ ሚሳይል ታጥቀው ሊሆን ይችላል፡ ወርውረው አንዲት አገር ሙሉ ሊያጠፉ ይችላሉ። አንዱ ጠፈርተኛ፡ ወጥቶ እዚያ ይቆማል። ከማድረግ ሊከለክላቸው የሚቻለው አንድ የለም። በፈለጉት… ጊዜና ሰዓት፡ በርግጥ ማድረግ ይችላሉ። ቢፈልጉ… ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ፡ አፈር ሊያደርጓት ይችላሉ። አንደኛው ማድረግ የሚችለው፡ ሌላኛውም ደግሞ፡ ማድረግ ይችላል። አያችሁ፡ ስለዚህ ነው የተሰማሙት፡ ይሁን እንጂ እንዲህ አይነቱ ሰምምነት ፍርሃት ውስጥ ይከታቸዋል።

110 ኃይላቸውን አንድ ላይ በማድረግ፡ አንድነት እየመሰረቱ ነው። ነጻው ዓለም፡ ኃይላቸውን ሁሉ አንድ በማድረግ ላይ ናቸው። ኮሙኒዝሞች ኃይላቸውን ሁሉ ከሩሲያ ጋር እያደረጉ ናቸው። ሁሉንም፡ ነገር ግን አንዳቸው ሌላኛው ይፈራዋል። አያችሁ፡ የሚያስፈራ ምልክት ነው። ትክክለኛ ነው። አገር አቀፍ ምልክት፡ እና ወዘተ ይህ ነው።

111 ቤተ ክርስትያኒቱም ግን፡ ጠፈርተኛ! የሆነ ምልክት ተቀብላለች፤ አሜን! ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በእሳት ዓምድ መልክ፡ በብሉይ ኪዳን እንደነበረ፤ ወደ ደማስቆ በሚወስደው መንገድ ከሳኦል ጋር በተገናኘ ጊዜ፡ የነበረው ኢየሱስ ዛሬም እዚህ ነው! እሱስ ምን ያደርጋል? ፍርኃት ያመጣልን? አንዱ ከሌላው አንድ የሚያደርግ፡ ፍቅር ያመጣል። አሜን! እርስ በእርስ እንድንተሳሰብ። እንደ ሙሽሪት አንድ እንሆን ዘንድ፡ የእግዚአብሄርን ፍቅር፡ የክርስቶስን አካል፡ ወደ እኛ በማምጣት አንድ ያደርገናል። ይህ እግዚአብሄር የሚያደርገው፡ ታላቅ አንድነት…

112 እነዚህ ቡድኖች **እዚያ** ካሉት ጋር ለመዋጋት፣ እነዚያም ቡድኖች **እዚያ** ካሉት ጋር ለመዋጋት፡ እርስ በእርሳቸው አንድነትን እየፈጠሩ ናቸው። እዚህ ጋር ደግሞ ቤተ ክርስትያን በሁለቱ መካከል ቆማለች፡ ምን እንደሚሆን ግን ጠብቁ፡ ከእነሱ ጋር በሕብረት አንድነት ታደርጋለች። ይህ ትክክለኛ ነው። አሁን፡ ግን፡ ፍርኃት እና አለመረጋጋት የሚያመጣ እንደሆነ እናያለን።

113 ቤተክርስትያን ግን፡ ሙሽራይቱ ግን፡ በአንዱ መንፈስ፡ ከእግዚአብሄር መንፈስ ስር፡ ከአንዱ አምላክ ጋር፡ በቅዱስ የእግዚአብሄር ጋብቻ፡ ለእግዚአብሄር የተቀደሰች ሙሽራ ለመሆን አንድ ሆናለች። ትክክል ነው፡ ሁሉም፡ የአካሉ ሕብረት ናቸው። ይህ አካል ሙሽሪት እንደ መሆናችን፡ እራሳችንን ሙሽሪት—ብለን እንደምንጠራው፡ እንደ ሙሽሪት ይጠባበቃል። ስለ ሙሽራይቱ አንድነት፡ ቤተ ክርስትያኒቱ ሕብረት እያደረገች ትገኛለች። እርስ በእርስ እንዳንለያይ፡ ፍቅርን በውስጣችን መፍጠር አለበት። በትክክል። እንዲህ ሲሆን፡ ሰዎች እንዲጸልዩ መለመን አያስፈልጋችሁም፡ እግዚአብሄርን እንዲያመልኩ መለመን አያስፈልግም፡ ትክክለኛ ነገር እንዲያደርጉ መለመን

አያስፈልግም። ለሌላው ነገር እስከማይሆኑ ድረስ፡ ከእሱ ጋር እጅግ በፍቅር ተይዘዋል።

114 እስኪ ምን ታስባላችሁ፡ አንዲት ቆንጆ ልጃ ገረድ፡ በፍቅር እጅግ የከነፈችለትን ቆንጆ ወጣት ለማግባት የተዘጋጀች፡ እሱ ማለት ለእሷ ከህይወቷ በላይ ከሆነ፡ እንደሚያገባት ስላወቀች ሴት ምን ይመስላችኋል? ሰርጉ እንደቀረበ፡ ይቺ ታናሽ እመቤት፡ የምታደርገውን፡ እኔ ልንገራችሁ “ወዲያ ወዲህ ትሯሯጣለች።” አያችሁ? ሁሉንም ነገር ታዘጋጃለች፡ ሙሉ በሙሉ ትማረክለታለች። በትክክል። እሷ ማድረግ የምትፈልገው፡ እሱን የሚያስደስት ነገር ብቻ ነው። በጣም ጥሩ፡ ቤተ ክርስትያንም እንዲህ መሆን አለባት፡ ህይወታችን በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሄር ዘንድ ይሰወር፡ በመንፈስ ቅዱስም ይታተም።

115 እዚህ ያስተማርኳችሁ ነገሮች፡ ስለ እነዚህ ምልክቶች እና እየሆኑ ያሉ የተለያዩ ነገሮች፡ አሁን ለመጨረስ ጊዜ የለኝም፡ ጌታ ቢፈቅድ ግን፡ በሌላ መልእክት እጨርሰዋለሁ። ነገር ግን በቤተክርስቲያን ውስጥ አንድ ትንሽ ነገር ገና ይጎድላል። ስለሆነም፡ ወደዚያ መግባት አለብን፡ እኔም ጫፍ ላይ ደርሻለሁ። አያችሁ? ቢሆንልን... መግባት ከቻላችሁ፡ ወደዚያ መድረስ አለብን። ይህ ብቻውን፡ ከሆነ ግን፡ ይህን አድርጉት። ምክንያቱ፡ የአንድነት ጊዜ በደጅ ነው፡ እግዚአብሄርም ቤተክርስትያንን አንድ ላይ ለንጥቀት—እያዘጋጃት ነው ወደ ታላቁ አንድነት ወደ ሰርጉ፡ እግዚአብሄር እና ሰው አንድ ወደሚሆኑበት ዘለአለማዊነት፣ የጊዜ ፈጣሪዎች ዘለአለማዊው ጋር አንድ ወደሚሆኑበት እያደራጃት ነው።

116 ከዚህ በፊት በሰው ልጅ ምሳሌ ተደርጎ ያውቃል። ሰዎችን ከዚህ ኃይል ጋር አንድ ለማድረግም፡ ህይወቱ መስጠት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽራም፡ ይሄን ኃይል ማውረድ ነበረበት። አሁን ደግሞ ቤተ ክርስትያን ወደ ክርስቶስ አካል ሕብረት በማድረግ ትገኛለች። ከጥቃቅን እግር ብረት ሁሉ፡ እራሷን ነጻ ማድረግ አለባት፣ በመካከላቸው ሕብረት በመፍጥር፡ እራሷን ማዘጋጀት፡ እና አንድ ማድረግ፣ አቤት፡ ፍቅር እና ደስታ፡ እና መንፈስ ቅዱስ በመካከላቸው ሲመላለስ። ኦህ፡ ማይ፡ እንዴት ያለ ዘመን ነው!

117 ዳክዬዎች መዘጋጀታቸውን ሰናይ፣ የዝይዎች መዘጋጀት ሰናይ፣ እንስሶች ሲዘጋጁ ተመልክተን... ንቦች ሲዘጋጁ፣ ከባድ ግፊት ስለ ሆነ፡ ደመናው ለመዝነብ ሲዘጋጅ፣ ሌላውን ሁሉ፡ እራሱን እንዴት እንዴት አንድ እንደሚያደርግ አይተነዋል። ሊግ ኦፍ ኔሽንን፡ ህዝቦች ሁሉ በአንድነት፡ እራሳቸውን በኮሙኒዝም አንድ እያደረጉ አይተናቸዋል። በምዕራቡ ዓለምም እራሳቸውን አንድ ሲያደርጉ አይተናቸዋል። ቤተ ክርስትያን እና ሌሎች ሁሉ፡ እራሳቸውን አንድ ሲያደርጉ አይተናቸዋል። በሌላው ዘመን እንዲህ ሊሆን፡ በፍጹም የማይቻል ነገር ነው፤ የዛሬ ሀያ አመት እንዲህ ሊሆን አይቻለውም ነበር፡ ሊሆን አይችልም። የዛሬ አስር አመት መሆን አይችል ነበር፡ አሁን መሆን አለበት። አያችሁ፡ ኢዝሞች እና ሌላ ነገሮች ወደዚህ ሁኔታ አልተገለጡም ነበር።

118 አሁን ንቁ! በፍጥነት፡ እራሳችሁን ቀሰቅሱ፡ የት እንዳለንም ተመልከቱ! የት ነን? እንደ ሰብአ ሰገል፡ ከቃል ጋር በመስመር ላይ ነን፡ የጌታ ብርሃንም በመንገዳችን ላይ በርቷል። ክብር ለእግዚአብሄር በአርያም

ይሁን። የምንወደውን ኢየሱስ ክርስቶስን ለሰጠን፡ ወደዚህም ቦታ ላደረሰን፡ ለእግዚአብሄር ክብር ይሁን። በደሙ ዋጋ የተገዛን... እኛ ለእርሱ፡ ህዝቡ ነን።

119 ኦህ፡ ማይ! የአንድነት ጊዜ ሲመጣ፣ በመንፈሱ ማሰሪያ እርስ በርሳችን ስንያያዝ፡ እናያለን፡ እኛም... መንፈሱ ይሆንን? አዎን፡ መንፈሱ ነው። ለምን? የራሱ ቃል ስለሆነ፡ እራሱም... የገዛ ቃሉ መንፈስ ነው። የተሰፋው መንፈስ በእናንተ ላይ ወርዶ እራሱን ሲያሳይ እና ሲገልጥ፤ ያው መንፈስ ነውን? ከሙሴ ጋር በምድረ በዳ የነበረው እርሱ ነው! በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የነበረው አንዱ እሱ ነው! በደማስቆ መንገድ ከሳኦል ጋር የተገናኘው እሱ ነው! እሱ ትናንትና፣ ዛሬ፣ እና ለዘላለም ያው ነው! እና ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል!

120 እናም ህዝቦች አንድ ሲሆኑ አየን፣ የቤተክርስቲያን መሪዎችን አብረው ሲሆኑ አየን፣ ኮሚኒዝምን ሲያብር አየን፣ ኢዝሞችን አንድ ላይ አየን፣ እነዚህን ሁሉ ነገሮች አይተናል፣ አሁን ግን ሙሽራይቱ ከቃሉ ጋር ስትዋሃድ እየናት። ኦህ፡ ማይ! ቅዱሳን በሕይወት ካሉት ጋር አንድ ለመሆን የሚነሡበት ጊዜ፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን የሚሄዱበት ጊዜ አሁን ነው።

121 በዚህ ምሽት፡ ከክርስቶስ ጋር አንድ እንድንሆን፡ እግዚአብሔር ይርዳን፡ እኛነታችንን ሁሉ ለእሱ አሳልፈን እንድናስገዛ፣ ያለን ሁሉ፡ በሙላት ነፍሳችንን፣ ስጋችንን፣ ሐሳባችንን፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሰጥተን፣ የአንድነትን ጊዜ እንጠባበቃታለን።

የጌታ መለከት ሲነፋ፡ ጊዜውም ሲፈጸም፣
የንጋት ብርሃን ይብራ፡ ለዘለአለም፣
በክርስቶስ ሆነው የተኙ ተነሥተው ወደ ሰማይ ሲሰበሰቡ፡
(ህያው ከሆነች ሙሽራ፡ አብረው ሲነጥቁ።)

122 አንድነቱን ተመልከቱት! ሁለቱ አንድ ይሆኑ ዘንድ፡ እግዚአብሄር ቤተ ክርስትያንን ከቃል ጋር፡ ቃልንም ከቤተ ክርስትያን ጋር አንድ ያደርጋል፣ "**ይህ** ይሁን በሉ፡ ይሆናል። **ይህ** ይደረግ በሉ፡ ይደረጋል። ይሄ ነው፡ በፊታችሁ ያለሁት እኔ ነኝ፡ የሚያረጋግጥላችሁ እኔ ነኝ፡ ከእናንተ ጋር ያለሁት እኔው ነኝ።" በጣም ጥሩ።

123 አሁን መለከት የሚነፋበት ጊዜ እንደሚመጣ አውቀናል፡ ያኔ የተኙት ቅዱሳንም፣ ያለ እኛ ፍጹማን ሊሆኑ አይችሉም፡ የእኛ ጥገኞች ናቸው (ዕብራውያን 11)፤ በሕብረት በመጡ ጊዜም፡ ከሕያዋን ጋር አንድ ይሆናሉ። ይህም ቤተ ክርስትያን ከቃል ጋር አንድ ትሆናለች፡ ቤተ ክርስትያንን እና ቃል ሕብረት ያደርጋሉ፡ አንድ ይሆናሉ። የሞቱት ቅዱሳን ሕያው ከሆኑ ቅዱሳን ጋር አንድ ለመሆን ሕብረት ያደርጋሉ፡ ከክርሰቶስ ጋር አንድ ለመሆን ወደ በጉ ሰርግ እራት፡ በሕብረት ይጓዛሉ።

124 ጊዜው አንድነት ነው፡ ምልክቶቹም በየቦታው ይበራሉ። ምልክቶቹ በሕዝብ ውስጥ፡ ምልክቶቹ በኮሚኒዝም ውስጥ ናቸው፡ በምዕራቡ ዓለም ምልክቶቹ አሉ፡ ምልክቶቹ በአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ውስጥም አሉ። ዛሬ ማታም ምልክቱ በመንፈስ ቅዱስ ጥላ ሥር እዚህ አለ፣ የእግዚአብሄር ቃልም እውነት እንደሆነ እያረጋገጠ ይገኛል። አሜን! የአንድነት ዘመን! የአንድነት ዘመን ምልክት!

ራሶቻችን ዝቅ እናድርግ።

125 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ በመካከለኛ-እድሜ ያለሁትን ሰው፡ እድሌን ሳየው፣ ምስኪኑን ልቤ በደስታ ይዘላል፡ ደግሞም፡ አንተ በዚህ ትውልድ መካከል ስትመጣ ማየት መታደሌ፡ ያቺ መለከት ስትነፋ፡ ህያው ሆኜ እና በዚህ ቆሜ ማየት መቻሌ፡ "እርኩሱም፡ ይርከስ። ጻድቁም፡ ይጽደቅ። ቅዱሱም፡ ይቀደስ።" ጌታ አምላኬ ሆይ!

126 በቅጽበተ ዓይን፡ በድንገት፡ በፊቱ መቆማችሁ ስታስቡት፡ ዓለም ምን እየተፈጸመ እንዳለ ሳታውቅ፡ እንደ አጋጣሚ ግን፡ በፊታችሁ ቆመው ስታዩአቸው፡ የተለዩአችሁ ወዳጆቻችሁ፡ ከእናንተ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስታዩአቸው አስቡት። እኛም በድንገት፡ በቅጽበት ዓይን እንለወጣለን፡ አብረንም፡ ጌታን አየር ላይ ለመቀበል፡ እንነጠቃለን። በዚያም ከእሱ ጋር፡ ለዘለአለም ለመኖር፡ በፍጹም ከህልውናው ላለመውጣት ሕብረት እናደርጋለን።

127 ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ከአንዱ መንፈስ ጋር አንድ መሆናችንን ሰናውቅ፡ እንዴት ይደንቃል። መንፈስ ቅዱስ፡ ቃሉን በእቅፉ አዝሎ፡ ወደ ውስጣችን የገባ፡ አንዱ መንፈስ። ከዓለም ተቆራርጦ፡ እራስህን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ ማድረግ፡ እንዴት ያለ ተአምር ነው። አንድ ቀንም፡ ክቡር ስጋውን በሚመስል ስጋ፡ በአካል መልክ፡ በሰርጉ እራት ገበታው ላይ ተገኝተን ከእርሱ ጋር በጋብቻ አንድ መሆናችንን ሰናስብ፡ በሚመጡት ዘመናት ሁሉ እንደ ሙሽሪት እና ሙሽራ፡ ፍጻሜ በሌለው ዘለአለም ከእርሱ ጋር እንኖራለን።

128 ጌታ አምላክ ሆይ፡ ይህ ለህዝቡ የተረት ሐሳብ ብቻ አይምሰላቸው፡ ነገር ግን ልዩ አይነት ረሃብ እና ጥማት በህዝቡ ላይ እስኪሰፍር ድረስ እውን ይሁን… ጋዜጣቸውን ሲያነቡ፣ ነገሮችን ሲመለከቱ… ሬድዮውን እና ዜናውን ሲያዳምጡ፣ የአንድነት ዘመን መሆኑ ይታያቸው። ምልክቶቹ ያንጸባርቁባቸው።

129 ጌታ እግዚአብሔር ሆይ በመጨረሻው ዘመን፡ ሴቶች ስለሚያደርጉት ነገር እንደተናገርነው፡ በመጨረሻው ዘመን ቤተ ክርስቲያን የምታደርገው፡ የቤተክርስቲያን ዘመናት ምን እንደሚሆን፡ እና ማኅተሞች ምን እንደሚሆኑ፣ እነዚህ ሁሉ ሌሎች ነገሮች። በኖኅ ዘመን እንደነበረ፡ አሁን አይተናል። በሰዶምና በሎጥ ዘመን እንደነበረ፡ የእግዚአብሔር መልአክ በሰው ሥጋ እራሱን ገልጾ፡ አየን፡ ያኔ እሱ ላም ስጋ በልቶ የላም ወተት ጠጥተዋል፡ ቂጣም ቆርሷል፡ ባለበት ሆኖ ከበስተጀርባው የሚደረግ ነገር መናገር ይችል ነበር። ኢየሱስም የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ እንዲሁ ይሆናል ብሏል።

130 ጌታ አምላክ ሆይ፡ ፒራሚዱን፡ እዚያ እንዴት እንዳሠራን፡ እና እነዚህን ነገሮች እንዴት እንደጨመርንበት አይተናል፤ ዋናውን የማዕዘን ድንጋይ እየጠበቅን በመጨረሻው-ዘመን ላይ መሆናችንን ተረድተናል። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! አባት ሆይ፣ ሰዎችን አሁን ቶሎ፡ እንድታነቃቸው፣ እና እንድትሰበሰበን፡ እንጸልያለን፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ እና እርሰበርሳችን አምላክዊ ፍቅር እና ክብር ይኑረን።

131 በውስጣችሁ ያረፈ ተስፋ የሌላችሁ አንዳንዶች ዛሬ ማታ እዚህ ካላችሁ፣ እጃችሁን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታችሁ እንዲህ በሉት፡ "ጌታ አምላክ ሆይ፡ ከአንተ ጋር አንድ አድርገኝ፣ ካንተ ጋር አንድ አድርገኝ"? እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ አንተንም፡ አንተንም እዎን። "አቤቱ ከአንተ ጋር፡ አንድ አድርገኝ።" እዎ! ኦህ፡ማይ!

አገሮች ፈረሱ፣ እስራኤል ተነቃቅታለች፣

132 እስራኤልን ተመልከቷት፡ በአንድነት ሕብረት አርጋለች። እስራኤል, ከመላው ዓለም, ራሳቸውን አንድ ለማድረግ መጥተዋል፡ ራሳቸውን አንድ ለማድረግ አሁን ህዝብ ሆነዋል። የተባበረ ሕዝብ ናቸው፡ በራሳቸው ባንዲራ፡ የራሳቸው ገንዘብ፡ የራሳቸው ሠራዊት፡ በሁሉ ነገር፡ ኖሩ ከተባለ፡ አሁን ነው። እስራኤል አንድ ሆናለች፣ ሮም አንድ ሆናለች፣ ቤተክርስትያንም አንድ ሆናለች። እና በዚያ ታላቅ ህብረት መምጣት፡ አሜን፡ ሙሽራይቱም አንድ ሆናለች። ምንድን ነው? ይህ ሁሉ ወደዚያ ምልክት፣ ወደ ዋናው ምልክት፣ ኢየሱስ እና ሙሽራው እንደ አንድ ተጣምረዋል።

133 ጌታ አባት ሆይ፡ ስለ ሕዝቡ የለመንኩህን በረከት ስጣቸው፡ እነሱ ይህን ፈልገው፡ እጆቻቸውን ሲያነሱ፡ በልብ እና በመንፈስ ከአንተ ጋር አንድ እንሁን። ጌታ አምላክ ሆይ፡ አንጻን እና የአንተው አርገን፡ ጌታ ሆይ፡ ስጠን። እኛ የምናውቀው እና ማድረግ የምንችለው፡ መጠየቅ ብቻ ነው። እናንተም አምናችሁ ከጸለያችሁ ትቀበላላችሁ ብለኸናል፡ ጌታ ሆይ፡ እኔ ይሄን እየጠበቅኩ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አመሠግንሃለሁ። አሜን።

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ፡
ቀድሞ ወዶኛልና፡
መዳኔንም ገዝቶልኛል
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

አሜን፡ ኦህ፡ ማይ!

እነሆ፡ ሙሽራው መጣ!
የእኩለ ሌሊት ጩኸት ሰማሁ!
በጩኸት ወደ ላይ እንሄዳለን፡ በጽናት ከጠበቅን፡
በሰማይ እሱን እናገኘዋለን።

ንቃና ጸልይ፡ ወንድሜ፡
ዘውድህን በማንም አይወሰድ፡
ደካሞችን እና ለብ ያሉትም
የሰርጉን ልብስ አይለብሱትም።

134 ትክክል ነው። ለእኩለ ሌሊት ጩኸት እንዘጋጅ። ባላሰባችሁት ሰዓት ውስጥ ይመጣል። ጩኸት ይኖራል፡ ይህ ግን ምስጢራዊ ስለሆነ፡ በማያምኑት መካከል አይደለም። ነገር ግን ይሄን እየጠበቁ ባሉ፡ በአማኞች መካከል ይሆናል፡ ከዋክብት በመሰመር ሲመጡ አይታችኋል? አያችሁ? ምን አመጣ? ልክ በመጀመርያ እንደሆነ። አያችሁ፡ ይሄው፡ ምልክቶቹ እየመጡ ናቸው።

የተባረከውን የመምጣቱን ምልክቶች አይተናል፡
እነሆ፡ የበለስ ቅጠሎች አረንጓዴ ሆኖዋል፡
የመንግሥቱ ወንጌል ለሕዝብ ሁሉ ደርሷል፤
እኛም ቀርበናል፡ መጨረሻው ሊታይ ችሏል.

ከዚያም በደስታ፡ ወጥተን፡ የተባረከ የመምጣቱ መልእክት እናበስራለን፣

135 ልክ ነው? ኦህ፣ “የተባረከ የመምጣቱን መልእክት አብስሩ!” እኛ ማድረግ ያለብን ይህንኑ ነው። ለሁሉም ንገሩ “ተዘጋጁ፣ እግዚአብሔርን ለመገናኘት ተዘጋጁ።” አሜን! እወደዋለሁ፡ አቤት፡ ሰወደው። አሁን፡ በእግራችን እንቁም። እርሰ በርሳችን ሰንከራከር፡ አጠገባችን ካለው ጋር እጅ እየተጨባበጥን፡ እንዲህ እንላለን፡

እሰክንገናኝ!

ተጨባበጡ፣ አሁን።

... እሰክንገናኝ!
በኢየሱሰ እግር ላይ እሰክንገናኝ ድረሰ፡
ድረሰ...

አስታውሱ፡ ሊጠራችሁ ይችላል፡ ቀጣዩ ሰብሰባችን በእግሩ ሰር ሊሆን ይችላል።

አቤት፡ ዳግም እሰክንገናኝ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን!

136 አሁን፡ እንደገና ከመገናኘታችን በፊት፡ እሁድ ጠዋት፡ ወይም እሮብ ምሽት ከመገናኘታችን በፊት፡ ይሂን አሰቡ፡ እንዲህ ሊሆን ይችላል... ታውቃላችሁ በመጀመሪያ፡ እከሌ የለም። ይሄኛው የለም፣ የሉም ጠፍቷል። አቤት፡ ባልሽ አለመኖሩ ሰታሰቢ፡ ወይም ሚሰትህ አለመኖሯ አሰበው፡ እና—የጆን ሚሰት ጠፋች፡ እና—እና—እና እነዚያ ህጻናት የሉም ጠፍቷል። ሁሉም ተፈጸመ (ምን ተፈጠረ? )፡ ከዚያ በኋላ እናንተ ቀርታችኋል!

አቤት፡ ሐጢአተኞች እጣ ፈንታቸው
ሲነገራቸው ለቅሶና ዋይታ ይሆናል፤
ወደ ዓለቶችና ተራራዎች ጮኹ፤ (እሰራኤል፡ ወደ ከተማይቱ፡ ወደ መቅደሱ ሲመለሱ እንደጮኹ።)
ጸለዩ ግን ጸሎታቸው በጣም ዘገየ። (መልእክቱን አልተቀበሉትምና።)

137 ወንድሜ፡ ሆይ፡ በጭራሽ እንዲህ አታድርግ። ምንም ብታደርጉ ለጥሪው በጀግንነት ቁሙለት! አዎን፡ ወዳጄ!

138 አሁን፡ እሰክንገናኝ ድረሰ፡ ይህን እናደርጋለን፡

የኢየሱሰን ሰም ከእናንተ ጋር ውሰዱ፡
ከድካም ሁሉ ጋሻ ነውና፤
ፈተናዎች ሲከቧችሁ፡ (ምን ታደርጋላችሁ? )
ቅዱሱን ሰም በጸሎት ተንፍሱ።

ድንቅ ሰም፡ ኦህ ውብ ነው!
የምድር ተሰፋ የሰማይ ደሰታ፡
ድንቅ ሰም፡ ኦህ እንዴት ውብ ነው!
የምድር ተሰፋ የሰማይ ደሰታ፡

139 እያንጎራጎር እንዳለን፡ ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ፡

ለኢየሱስ ስም እሰግዳለሁ፡
በእግሩ ስር እዘረራለሁ፡
ለነገሥታቱ ንጉሥ በሰማይ... ዘውድ ጭናለሁ፡
ጉዟችን ሲጠናቀቅ። (አንድ ቀን፡ ይሆናል።)
ኦህ ድንቅ ሰም፡ (ድንቅ ሰም!) ኦህ ውብ ነው!

እንደገና እስክንገናኝ፡ እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን።

የምድር ተሰፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ሰም፡ ኦህ ውብ ነው! (ውብ ነው!)
የምድር ተሰፋ የሰማይ ደስታ።

**የአንድነት ዘመን እና ምልክቱ** AMH63-0818

(The Uniting Time And Sign)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ነሐሴ 18፡ 1963፡ እሁድ ማታ፡ በጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና፡ በዩ. ኤሰ. ኤ. ከሚገኝ ብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈለጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org